# እፎይ አዲስ ዘመን

ዓርብ

83ኛ ዓመት ቁጥር 193 መጋቢት 13 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







## “የኢትዮጵያ ምልዑነት ሊረጋገጥ የሚችለው ሁሉም እምነት፣ ባህልና ታሪክ በልክ ሲቀመጡ ነው”

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

ገጽ 4



## “የኢትዮጵያን ታላቅነት ጠብቆ ለትውልድ የሚያስተላልፍ የመከላከያ ሠራዊት ተገንብቷል”

- ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ
የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም



**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያን ታላቅነት ጠብቆ ለትውልድ የሚያስተላልፍ የመከላከያ ሠራዊት ተገንብቷል ሲሉ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ ገለጹ።

የኢፌዴሪ መከላከያ ዋር ኮሌጅ ያሰለጠናቸውን ጄነራል መኮንኖችንና ከፍተኛ መኮንኖችን ትናንት አስመርቋል።

በወቅቱ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ እንደተናገሩት፤ መከላከያ ሠራዊት የኢትዮጵያን ታላቅነት የሚመጥን እንዲሆን የአሥር ዓመት ስትራቴጂክ እቅድ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ እየተደረገ ነው። ከለውጡ በኋላ ሠራዊቱን ለመገንባት በተሠሩ ሥራዎች የኢትዮጵያን አንድነትና ሉአላዊነት የማያስደፍር ጀግና

“የኢትዮጵያን ታላቅነት ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል


# አሳሳቢ እየሆነ የመጣው የድምጽ ብክለት

**ዜና ሐተታ**
**ዳግማዊት አበበ**

በዓለማችን ከተሞች እየተስፋፉና የሕዝብ ቁጥር እየጨመረ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ ብክለቶች እያጋጠሙ ይገኛል፡፡ ከእነዚህ የአካባቢ ብክለቶች አንዱ የድምጽ ብክለት ተጠቃሽ ነው፡፡ የድምጽ ብክለት የዓለም ጤና ድርጅት ባወጣው መረጃ መሠረት ከአየር ብክለት ቀጥሎ በሁለተኛ ደረጃ የጤና ጉዳት የሚያመጣ መሆኑ ተገልጿል፡፡ በሀገራችንም በተለይ በአዲስ አበባ ይህ ችግር በስፋት ይስተዋላል፡፡

የድምጽ ብክለት ሁሉንም ማህበረሰብ የሚጎዳ ቢሆንም በዋናነት ግን ኑሯቸውን ወይም ሥራቸውን

አሳሳቢ እየሆነ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# የአዳዲስ ኤምባሲዎች መከፈት መዲናዋ የዓለም የዲፕሎማሲ ማዕከል ሆና እንድትቀጥል ያስችላል


ፎቶ:- ገባቦ ገብሬ
አቶ ነብዩ ተድላ

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ:- የአዳዲስ ኤምባሲዎች መከፈት አዲስ አበባ የዓለም የዲፕሎማሲ ማዕከል ሆና እንድትቀጥል የሚያስችል መሆኑን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በሳምንቱ የተከናወኑ ዓበይት የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴዎችን በማስመልከት ለሀገር ውስጥና ለውጭ ሀገር መገናኛ ብዙኃን ትናንት ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጥቷል።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ አቶ ነብዩ ተድላ በወቅቱ እንደገለጹት፤ ባለፈው ሳምንት ሁለት አዳዲስ ሀገራት በአዲስ አበባ ኤምባሲ ከፍተዋል። በዚህም በአዲስ አበባ ኤምባሲያቸውን የከፈቱ ሀገራት ቁጥር 134 ደርሷል። ከዚህ ውስጥ 52 የሚሆኑ የአፍሪካ ሀገራት

የአዳዲስ ኤምባሲዎች ... ወደ ገጽ 2 ዞሯል







# በቲቢ በሽታ ከተያዙ ታማሚዎች 20 ሺህ የሚሆኑት ወደ ሕክምና ማዕከላት አይሄዱም

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ በቲቢ ከተያዙ 156 ሺህ ታማሚዎች 20 ሺህ የሚሆኑት ወደ ሕክምና ማዕከላት አይሄዱም ሲል ጤና ሚኒስቴር አስታወቀ።

የአዲስ አበባ ከተማ ጤና ቢሮ እና የዓለም ጤና ድርጅት በመተባበር ያዘጋጁት የቲቢ በሽታ የግንዛቤ ማስጨበጫ የግማሽ ቀን ስልጠና ትናንት ለሚዲያ ባለሙያዎች ተሠጥቷል።

በስልጠናው ላይ የተገኙት በጤና ሚኒስቴር የቲቢ፣ የስጋ ደዌ እና ሌሎች የሳንባ በሽታዎች መከላከልና መቆጣጠር ዴስክ ኃላፊ አቶ ታዬ ለታ እንደተናገሩት፤ በኢትዮጵያ በዓመት 156ሺ የቲቢ ታማሚዎች አሉ ተብሎ ይታሰባል። ከነዚህ ውስጥ 20 ሺህ የሚሆኑት ወደ ሕክምና ተቋም የማይመጡ እና በማህበረሰቡ ውስጥ የሚገኙ ሲሆን፤ ከዚህም ውስጥ 16 ሺህ የሚሆኑት ታማሚዎች በበሽታው ምክንያት ለህልፈት ይዳረጋሉ።

ጤና ሚኒስቴር በሽታውን መከላከል ላይ ትኩረት አድርጎ እየሠራ መሆኑን ጠቁመው፤ በዋናነት ስለበሽታው መተላለፊያ መንገዶች ግንዛቤ በመፍጠር፣ የግል ተቋማትን ያማከለ ሕክምና እና ምርመራ ሥራ እየተከናወነ መሆኑን ተናግረዋል።



**አቶ ታዬ ለታ**

የበሽታው ተጋላጭ የሆኑት በተለይ በማዕድን ማውጫዎች፣ በካምፖች እንዲሁም በዩኒቨርሲቲዎች አካባቢዎች የሚገኙት ሰዎች መሆናቸውን አስረድተዋል። የበሽታውን ስርጭት ለመቀነስ ትኩረት ተደርጎ እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል።

እንደ ኃላፊው ገለጻ፤ በኢትዮጵያ አሁን ካለው የቲቢ በሽታ ታማሚ ቁጥር በእአአ 2030 ወደ 108 ሺ ለመቀነስ እንዲሁም በእአአ 2035 ቲቢ የማህበረሰቡ የጤና ችግር በማይሆንበት ደረጃ ለማድረስ እየተሠራ ነው። የቲቢ በሽታን ለመመርመር የሚረዱ አዳዲስ መሳሪያዎችም ጥቅም ላይ እየዋሉ ነው።

በሽታውን ለመከላከል በሚደረገው ርብርብ የሚዲያ ባለሙያዎች ሚናቸው ከፍተኛ መሆኑን የገለጹት ኃላፊው፤ ኅብረተሰቡ ስለበሽታው መተላለፊያ መንገዶች እንዲያውቅ ግንዛቤ በመፍጠር የሚዲያ ባለሙያዎች ኃላፊነታቸውን መወጣት እንዳለባቸው ተናግረዋል። የሚዲያ ተቋማትም ማህበራዊ ኃላፊነታቸዉን እንዲወጡ አሳስበዋል።

አብዛኛው የቲቢ በሽታ ምልክት ደረቅ ሳል፣ ክብደት መቀነስ፣ የምግብ ፍላጎት መቀነስና የሌሊት ላብ መሆኑን የተናገሩት አቶ ታዬ፤ ኅብረተሰቡ እነዚህን ምልክቶች ሲያስተውል በአፋጣኝ ወደ ጤና ተቋም በመሄድ የቲቢ ምርመራ እንዲያደርግ ጠይቀዋል።

ዓለም አቀፍ የቲቢ ቀን መጋቢት 15 "የቲቢ በሽታን መግታት እንችላለን" በሚል መሪ ቃል በተለያዩ ዝግጅቶች ይከበራል። ስልጠናው የቲቢ በሽታ ምንነት፣ አይነቶች እና መከላከያ መንገዶች ላይ ያተኮረ ሲሆን፤ ከተለያዩ ሚዲያ ተቋማት የመጡ ጋዜጠኞች ተሳትፈዋል።

# ማህበሩ በሦስት ሀገራት ተግባራዊ የሚደረግ ፕሮጀክት አስጀመረ

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማህበር ከኦስትሪያ የልማት ትብብርና ቀይ መስቀል በተበረከተ አራት ሚሊዮን ዩሮ በጀት በኢትዮጵያ፣ በሩዋንዳና ዩጋንዳ በፆታዊ እኩልነትና አካታችነት ላይ ትኩረት አድርጎ የሚሰራ ስካይ በርድ ሁለት የተሰኘ ፕሮጀክት አስጀመረ።

በማስጀመሪያ ሥነሥርዓቱ ላይ የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር ፕሬዚዳንት አቶ አበራ ቶላ እንደገለፁት፤ የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር ካለፉት ዓመታት ጀምሮ ከኦስትሪያ ቀይ መስቀል ጋር በመተባበር በርካታ ሰብዓዊ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል።

ማህበሩ ከተለያዩ መሰል ተቋማት ጋር በጋራ በመስራት የሀብት ድጋፎችን በማግኘት የቆመለትን ዓላማ የማሳካት ፍላጎት አለው ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ በኢትዮጵያ በነበሩ ግጭቶች ማህበሩ ሠራተኞቹን ጨምሮ በርካታ ንብረቶቹን እንዳጣ ጠቁመዋል።

የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማህበር ዋና ፀሐፊ አቶ ጌታቸው ታአ እንደገለጹት፤ እስከ ህዳር 2029 ተግባራዊ የሚደረገው ይህ ፕሮጀክት የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትና አካታችነትን ማዕከል በማድረግ ከኦስትሪያ የልማት ትብብርና ከኦስትሪያ ቀይ መስቀል በተበረከተ አራት ሚሊዮን ዩሮ በጀት በኢትዮጵያ፣ በሩዋንዳና ዩጋንዳ ላይ ተግባራዊ ይደረጋል።

በዚህም ለኢትዮጵያ 900 ሺህ ዩሮ የተመደበ ሲሆን፤ በኦሮሚያ ክልል በኢሉባቡርና ምዕራብ አርሲ ዞን ኢንዲሁም በሲዳማ ክልል እንደሚተገበር ተናግረው፤ ለጋሾች ላደረጉት ድጋፍ እና ቁርጠኝነት የላቀ ምስጋና አቅርበዋል።

እንደ አቶ ጌታቸው ገለጻ፤ አላማውም የቀይ መስቀል ብሔራዊ ማህበራትን በጥበቃ፣ በሥርዓተ-ፆታ እኩልነትና አካታችነት ያላቸውን ተቋማዊ አቅም ማጠናከር፣ ሴቶችን በውሳኔ ሰጭነትና በመሪነት ደረጃ ያላቸውን ተሳትፎ ማሳደግ፣ እንዲሁም የሴቶችን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደህንነትን ማጎልበት ይጠቀሳሉ።

ይህም የሚከናወነው በድርጅታዊ ግምገማ፣ በአቅም ግንባታ ወርክሾፖች፣ የሥርዓተ-ፆታ ትንተና፣ የማህበረሰብ አመራር ልማት እና የሴቶች ልዩ ፍላጎቶችን ለማሟላት የተዘጋጁ ንዑስ-ድጋፍ ፕሮጀክቶችን በመተግበር መሆኑን ዋና ፀሐፊው አመልክተዋል።

ሴቶችና ልጃገረዶች በማህበረሰባቸው ውስጥ ንቁ የለውጥ ወኪሎች እንዲሆኑ ለማበረታታት ድጋፍ እናደርጋለን ያሉት አቶ ጌታቸው፤ ይህ ፕሮጀክት የፆታ እኩልነትን ብቻ ግብ ያደረገ ሳይሆን እያንዳንዱ ግለሰብ ለመልማት የሚያስፈልጉትን አገልግሎቶች የሚያገኙበትን የወደፊት ጊዜ ለመፍጠር እንደሚሰራ ጠቁመዋል።

የኦስትሪያ ቀይ መስቀል የኢትዮጵያ ተወካይ አቶ ተመስገን አበበ በበኩላቸው፤ ፕሮጀክቱ በሁለት ዙሮች እየተተገበረ ያለ ሲሆን፤ የመጀመሪያው ላለፉት አምስት ዓመታት በምሥራቅ አፍሪካ በኢትዮጵያ፣ በኬንያ፣ በደቡብ ሱዳን፣ በሩዋንዳ፣ በኡጋንዳና በሌሎችም ሀገራት ተግባራዊ ተደርጎ 210ሺህ ዜጎችን ተጠቃሚ ማድረግ ችሏል ነው ያሉት።

"የሁለተኛው ዙር ፕሮጀክት በኢትዮጵያ፣ በሩዋንዳና ዩጋንዳ ለቀጣይ አምስት ዓመታት ተግባራዊ የሚደረግ ነው፤ በጀቱም እንደየፕሮጀክቱ አተገባበርና አስፈላጊነት ለሀገራቱ የሚካፈል ይሆናል" ያሉት አቶ ተመስገን፤ በሦስቱ ሀገራት የሚገኙ 200ሺህ ዜጎችን ተጠቃሚ ለማድረግ መታሰቡን ተናግረዋል።

በማስጀመሪያ መርሀ ግብሩ ላይ በኢትዮጵያ የኦስትሪያ አምባሳደርን ጨምሮ የሩዋንዳና ዩጋንዳ ቀይመስቀል ማህበራት ተወካዮች ተገኝተዋል።

# በክልሉ በ101 ግብር ከፋዮች ላይ ርምጃ ተወሰደ

**ሶሎሞን በየነ**

አዲስ አበባ፡- በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ባለፉት ሰባት ወራት የታክስ ሕጉን በጣሱና ግብር ሲያጭበረብሩ በተገኙ 101 ግብር ከፋዮች ላይ ሕጋዊ ርምጃ መውሰዱን የክልሉ ገቢዎች ቢሮ አስታወቀ። በተከናወነው የታክስ ሕግ የማስከበር ሥራም ገቢ ሳይደረግ የቆየ 11 ነጥብ 4 ሚሊዮን ብር ወደ መንግሥት ካዝና ገቢ ተደርጓል።

የክልሉ ገቢዎች ቢሮ ምክትል ኃላፊና የታክስ ሕግ ተገዥነት ዘርፍ ኃላፊ ወይዘሮ ትዕግስት በላይ በተለይ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደገለጹት፤ ቢሮው ከክልሉ ፍትሕ፣ ሰላምና ፀጥታ ቢሮዎች እንዲሁም ፖሊስ ኮሚሽን ጋር በመተባበር እየሠራ ይገኛል።

በዚህም በክልሉ መሰብሰብ የሚገባውን ታክስ በአግባቡ ለመሰብሰብና የታክስ ሥርዓቱን ከሕገ ወጦች ለመታደግ ባለፉት ሰባት ወራት የተደራጀ የታክስ ሕግ የማስከበር ሥራ ሲያከናውን ቆይቷል።

በተከናወነው የተደራጀ የታክስ ሕግ የማስከበር ሥራ የታክስ ሕጉን በጣሱና ግብር ሲያጭበረብሩ በተገኙ 101 ግብር ከፋዮች ላይ ሕጋዊ እርምጃ በመውሰድ፤ ገቢ ሳይደረግ የቆየ 11 ነጥብ 4 ሚሊዮን ብር ወደ መንግሥት ካዝና ገቢ ተደርጓል።

እንደ ኃላፊዋ ማብራሪያ፤ ደረሰኝ በማይቆርጡ የንግድ ድርጅቶች፣ ሕገ ወጥ ደረሰኝ በሚያሳትሙና በሚያቀርቡ ግብር ከፋዮች፣ ያገኙትን ገቢ ወይም ሽያጭ በሚደብቁ እና ሕጋዊ ፈቃድ ሳይኖር በሀሰተኛ ንግድ ፈቃድ ሲሠሩ በተገኙ ላይ ርምጃ ተወስዷል።

በተጨማሪም የኢንቨስትመንት ይዞታ ሽያጭ ከትክክለኛው ዋጋ በታች አሳንሶ በሚያሳውቁ፣ በሞተ ሰው ስም ድርጅቱን ለረጅም ዓመታት ሲያንቀሳቅሱና በአንድ ቤት ውስጥ በሦስት ሰው ስም የደረጃ "ሀ" ግብር ከፋይ ሆኖ ሲሠሩ በተገኙ ላይ ቅጣት ተጥሏል።

ከሁለት በላይ በሆነ ቲን /TIN/ የንግድ ማጭበርበር ሲያከናውኑ፣ ባልተሰጠ ስልጣን በከተማ ካቢኔ የግብር ምህረት በተደረገላቸው ላይ በታክስ ኢንተለጀንስ መረጃ ተሰብስቦ ርምጃ እንዲወሰድ ተደርጓል።

በዚህም በአጠቃላይ በ101 ግብር ከፋዮች ላይ ሕጋዊ እርምጃ በመውሰድ ከአምስት ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ ተሰብስቧል።

ከካርኒ ምርመራ አራት ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ብር ወደ መንግሥት ካዝና ተመላሽ መደረጉንና ከማህደር ጥራት ደግሞ ሁለት ነጥብ አንድ ሚሊዮን ብር ግኝት መገኘቱን ኃላፊዋ ጠቁመዋል።

ባለፉት ሰባት ወራት በተከናወነው የተቀናጀ የታክስ ሕግ የበላይነት የማስከበር ሥራ በድምሩ ገቢ ሳይደረግ የቆየ 11 ነጥብ 4 ሚሊዮን ብር ወደ መንግሥት ካዝና ገቢ መደረጉን ተናግረዋል።

"የታክስ ማጭበርበር ሥራ ላይ የተሰማሩ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች መንግሥት ከዘርፉ ማግኘት የሚገባውን ገቢ በመደበቅ የመንግሥት ካዝናን የሚያራቁቱና የሕዝብን ልማት የሚያስተጓጉሉ ናቸው" ሲሉ ገልጸዋል።



**ወይዘሮ ትዕግስት በላይ**

ለነዚህ የሕዝብ ልማት ጸር የሆኑ አካላት ተባባሪና ለግል ጥቅማቸው የቆሙ 16 የውስጥ ባለሙያዎች ላይም አስተዳደራዊና ሕጋዊ ርምጃ መወሰዱን አስረድተዋል።

ከላይ የተጠቀሱ በታክስ ሕጉ ላይ የታዩ ጥሰቶችና ማጭበርበሮች በሁሉም የክልሉ ስድስቱም ዞኖች መታየታቸውን ነው ኃላፊዋ ያመላከቱት።

በቀጣይም የታክስ ሕግ ማስከበር ተግባሩ እንደ አንድ የአሠራር ሥርዓት ተደርጎ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት በሕገወጦች ላይ የሚወሰደው ርምጃ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ወይዘሮ ትዕግስት ገልጸዋል።

# የአዳዲስ ኤምባሲዎች መከፈት መዲናዋ የዓለም...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ኤምባሲዎች ናቸው ።

በቅርቡ በአዲስ አበባ አርሜኒያና ኬፕቨርዴ አዲስ ኤምባሲ ከፍተዋል ያሉት ቃል አቀባዩ፤ ይህም አዲስ አበባ ከዓለም የዲፕሎማሲ ማዕከላት አንዷ ሆና የመቀጠል ጉዞዋን የሚያጠናክር መሆኑን ተናግረዋል።

ወዳጅነት ማብዛት፣ ነባር ግንኙነትን አጠናክሮ የማስቀጠልና አዳዲስ የትብብር ምዕራፎችን ከተለያዩ ሀገራት ጋር የመፍጠር ሥራዎች በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርና በሚሲዮኖች በኩል ተጠናክሮ መቀጠሉንም አመልክተዋል።

አዳዲስ ኤምባሲዎችን የሚከፍቱ ሀገራት ቁጥር እየጨመረ ነው ያሉት ቃል አቀባዩ፤ ቢሯቸውን በአዲስ አበባ የሚከፍቱ የተለያዩ ዓለም አቀፍ ተቋማት በየዓመቱ እየጨመረ መጥቷል ብለዋል።

ይህም አዲስ አበባን ከኒዮርክና ጄኔቫ ከመሳሰሉት ታላላቅ የዲፕሎማሲ መዲናዎች ተርታ እንዳሰለፋት ጠቁመው፤ የአዲስ አበባ የዲፕሎማሲ መዲናነት የሀገራችንን ብሔራዊ ጥቅምና ክብር የሚያጎናጽፍ በመሆኑ ወደፊት መሰል ሥራዎች ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ ገልጸዋል።

እንደ አቶ ነብዩ ገለጻ፤ ባለፈው ሳምንት 17 የሚሆኑ የተለያዩ ሀገራት ተተኪና አዲስ ተሿሚ አምባሳደሮች ለፕሬዚዳንት ሣህለወርቅ ዘውዴ የሹመት ደብዳቤያቸውን አቅርበዋል። የሹመት ደብዳቤያቸውን ካቀረቡት ሀገራት መካከል አዲስ ኤምባሲያቸውን የከፈቱት ኬፕቨርዴና አርሜኒያ ይገኙበታል።

ቀደም ሲል ከአዲስ አበባ ጋር ግንኙነት ያልነበራቸው ሀገራት ጭምር የሁለትዮሽና የባለብዙ ወገን ግንኙነት ሥራዎችን እየሠሩ መገኘታቸውን የጠቆሙት ቃል አቀባዩ፤ ይህ የሚያሳው አዲስ አበባ የዲፕሎማሲ መዲናነቷን አስጠብቃ እየተጓዘች ነው ሲሉ ገልጸዋል።

በየጊዜው ሁለንተናዊ አቅሟን በማሳደግ ለዲፕሎማቲክ ማህበረሰቡ ምቹና ተወዳዳሪ እንድትሆን ለማድረግ እየተሠራ መሆኑን አመልክተዋል።

በተያያዘ በሳምንቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አምባሳደር ታዬ አጽቀሥላሴ ከበርካታ ሀገራት ተወካዮች ጋር መወያየታቸውን በመግለጽ በቀጣይ ሳምንት የኢትዮጵያን ዲፕሎማሲ የሚያጠናክሩ ሥራዎች እንደሚሠሩ ጠቅሰዋል።

አቶ ነብዩ ተድላ አዲስ የተሾሙ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ ሲሆኑ፤ በሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭ በተለያዩ እርከን ላለፉት 22 ዓመታት በውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት አገልግለዋል። እንዲሁም ለሁለት ዓመት ያህል በምክትል ቃል አቀባይነት ሠርተዋል።

ዜና

# በመካከለኛው የድንጋይ ዘመን ሰው ከአፍሪካ ወደ ሌሎች አህጉራት መሻገሩ በጥናት ተረጋገጠ

## - ጥናቱ ኢትዮጵያን በይበልጥ የመካነ ቅርስ ጥናት ማዕከል እንድትሆን ያደርጋታል

**መስከረም ሰይፉ**


አዲስ አበባ፡- የመካከለኛው ድንጋይ ዘመን የሰው ልጅ ወንዝ ተከትሎ ከአፍሪካ ወደ ሌሎች አህጉራት እንደተሻገረ በጥናት መረጋገጡን የኢትዮጵያ ቅርስ ባለስልጣን አስታወቀ። ጥናቱ ኢትዮጵያን በይበልጥ የመካነ ቅርስ ጥናት ማዕከል እንድትሆን ያደርጋታል ተብሏል።

የባለስልጣኑ ምክትል ዳይሬክተር ኤልያስ ሽኩር በሰጡት መግለጫ፤ የመካከለኛው ድንጋይ ዘመን ሰው ደረቅ የአየር ንብረት ተቋቁሞ ወንዞችን እንደ መሻገሪያ በመጠቀም ከአፍሪካ ወደ ሌሎች አህጉራት እንደተጓዘ ላለፉት 22 ዓመታት በተደረገ ጥናት መረጋገጡን ገልጸዋል።

ጥናቱ በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ በሽንፋ መተማ አካባቢ ረባዳ ቦታዎች መደረጉን አስታውቀው፤ ጥናቱ ኢትዮጵያ የሰው ዘር መገኛ ብቻ ሳትሆን ዘመናዊ ሰው ለመጀመሪያ ጊዜ ሞቃታማ አየር ተቋቁሞ ከአፍሪካ ወደ ሌላ አህጉር መሻገሩን የሚያሳይ የሳይንስ ግኝት መካነ ቅርስ መሆኗንም አረጋግጧል ብለዋል።

የጥናቱ ቡድን መሪ ሙሉጌታ ፍሰሃ (ዶ/ር) እንደተናገሩት፤ ጥንታዊ ሰዎች ከአፍሪካ ወደ ሌሎች አህጉራት መቼና እንዴት እንደሄዱ የሚያሳይ ጥናት አልነበረም።

ለዚህ ችግር አንዱ መንስኤ የነበረው ከአፍሪካ ወደ ሌሎች አህጉራት መሸጋገሪያ የሆኑት የቀይ ባህርና የሜዲትራንያን ባህር የመሬት መሸጋገሪያ ድልድዮች የሚገኙት ሰፋፊ በረሀማ ቦታዎች አልፎ ስለሆነ ሰዎቹ የሚጠቀሟቸው ምግቦች የሚገኙት ደግሞ በጫካና




በለምለም ቦታዎች በመሆኑ በረሀውን መሻገር አይችሉም የሚል እሳቤ ስለነበር ነው ሲሉ አስረድተዋል።

እንደ ተመራማሪው ገለጻ፤ ጥንታዊ ሰዎች የድንጋይ መሳሪያዎችን በመጠቀም በአካባቢው ይገኙ የነበሩት እንስሳትን በማደንና ባልደረቁ ኩሬዎች ይኖሩ የነበሩ እንደ አሳና የመሳሰሉትን በመመገብ ፤በረሃማ የአየር ንብረት ተቋቁመው የመኖር ባህሪይ አዳብረው እንደነበር አዲሱ ጥናት አረጋግጧል።

በአካባቢው የነበረው ምግብ ሲያልቅባቸውም ከኩሬ ወደ ኩሬ በመሸጋገርና ወንዝ በመከተል በረሃማ ቦታዎች መሻገር እንደቻሉ መረጋገጡን ገልጸዋል።

ከዚህ በተጨማሪም በኢንዶኖዢያ ሰማትራ የፈነዳዉ የእሳተ ጎመራ አመድ በአካባቢዉ ባሉት ንብርብር አለቶች መገኘቱ ገልፀው፤ በሽንፋና መተማ ረባዳ ቦታዎች ይኖሩ የነበሩ ሰዎች ይህ እሳተ ጎመራ የፈጠረዉን የአየር ንብረት ጫና ለመቋቋም በኩሬዎች የሚያገኟቸውን ምግቦች



ኤልያስ ሽኩር

ይጠቀሙ እንደነበር አንስተዋል።

ከዚህ ባለፈ በአካባቢያቸው የነበረው ምግብ ሲያልቅም ወንዝ እየተከተሉ ከቦታ ቦታ ይንቀሳቀሱ እንደነበረ መረጃው እንደሚያሳይ አብራርተዋል።

ዶክተር ሙሉጌታ እንዳመላከቱት፤ በጥናቱ ዘመናዊ ሰዉ ከአፍሪካ አህጉር ወደ ሌሎች አህጉራት መቼና እንዴት እንደተሻገረ እስካሁን ላልተመለሱ ጥያቄዎች ምላሽ የሰጠ ነው።

# አርብቶ አደሮች የጤና አገልግሎት እንዲያገኙ አዲስ ስትራቴጂ ተነድፏል

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- በአፋር ክልል የሚገኙ አርብቶ አደሮች የጤና አገልግሎት እንዲያገኙ የሚያስችል ስትራቴጂ ተነድፎ እየተሠራ መሆኑን የክልሉ ጤና ቢሮ ገለጸ።

በክልሉ ጤና ቢሮ የማህበረሰብ ተሳትፎና ጤና ኤክስቴንሽን ዴስክ አስተባባሪ አቶ ኢሴ ዶጋ እንደገለጹት፤ አብዛኛው የክልሉ ማህበረሰብ አርብቶ አደር እንደመሆኑ ወደተለያዩ ቦታዎች በሚዘዋወርበት ወቅት የጤና ኤክስቴንሽን አገልግሎት የሚቋረጥበት ሁኔታ ነበር።

ይህም የጤና ኤክስቴንሽን ሥራውን በተፈለገው ደረጃ ለማሳደግ ተግዳሮት እንደሆነ የገለጹት አስተባባሪው፤ ችግሩን ለመፍታት አዲስ የአሠራር ሥርዓት ተዘርግቷል ሲሉ አስረድተዋል።

እንደ አቶ ኢሴ ገለጻ፤ የክልሉ ማህበረሰብ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ በሚንቀሳቀስበት ወቅት አንድ መሪ አለው። የሚንቀሳቀሱት አርብቶ አደሮች የት እንደሚሄዱ፣ መቼ እንደሚነሱ እና የጤና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ተጠቃሚዎች እንማን እንደሆኑ ያውቃል።

መሪው የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም አካል በመሆን፤ ከኤክስቴንሽን ባለሙያው ጋር ተናቦ ይሠራል ያሉት ኃላፊው፤ አገልግሎቱን ያልወሰዱት እንዲወስዱ ያደርጋል። በተጨማሪም የጤና ችግር ሲፈጠር ለሚመለከተው አካል ይጠቁማል ሲሉ አስረድተዋል።

አሠራሩ በክልሉ በአራት ወረዳዎች የተጀመረ መሆኑን ጠቅሰው፤ ከጤና ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የበለጠ ለማሳደግ እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል።

በተጨማሪም ከዚህ በፊት በክልሉ ማኀበረሰብ ዘንድ የሚዘወተሩ ባህሎችን ለጤና ሥራ እንደሚጠቀሙበት ተናግረዋል።

አሁን ላይ በክልሉ 769 ያህል የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች እንዳሉ ያስረዱት አቶ ኢሴ፤ ሆኖም ለባለሙያዎቹ የሚከፈለው ክፍያ ዝቅተኛ መሆን በሥራው ላይ እክል እየፈጠረ ነው ብለዋል።

ችግሩን ለመፍታት ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ጋር በመወያየት አዳዲስ ባለሙያዎችን የመተካት ሥራ



አቶ ኢሴ ዶጋ

እየተሠራ ይገኛል ሲሉ ተናግረዋል።

አቶ ኢሴ አያይዘው እንደገለጹት፤ በአሁኑ ወቅት በክልሉ ከዚህ በፊት 16 የነበሩት የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጆች፤ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች እና የአዕምሮ ጤና አገልግሎት ተጨምሮ 18 ደርሰዋል።

የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ከቦታ ቦታ በመዘዋወር እና በተቋም ደረጃ የምርመራ አገልግሎት እየሰጡ ይገኛል። በዋናነት ግን የሚሰሩት ማህበረሰቡን በማሰልጠን ወደ ሕክምና ተቋማት መጥቶ ሕክምና እንዲያገኝ ማድረግ ላይ ነው ብለዋል።

በዚህ ረገድ የጤና ኤክስቴንሽኖች ከቦታ ቦታ በመዘዋወር ከ370 በላይ የሚሆኑ ሰዎች 18ቱን ፓኬጆች አሰልጥነው እንዳስመረቁ ተናግረዋል።

የተመረቁትም ያገኙትን ትምህርት ለሌሎች ሞዴል ቤተሰቦች የሚያካፍሉ ሲሆን፤ እስካሁን ከ379 ሺህ በላይ ሞዴል ቤተሰቦች ስልጠና አግኝተዋል ሲሉ አስረድተዋል።

# በደን ጥበቃ የተሠሩ ሥራዎች የአርሶ አደሩን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ችለዋል

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ እየተከናወኑ ያሉ የደን ልማትና ጥበቃ ሥራዎች የአርሶ አደሩን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ መሆናቸው ተገለጸ።

ዓለም አቀፉን የደን ቀን በማስመልከት የፓናል ውይይት ትናንት ተካሂዷል።

የኢትዮጵያ ደን ልማት ምክትል ዋና ዳይሬክተር ሞቱማ ቶሌራ (ዶ/ር) በወቅቱ እንደተናገሩት፤ በደን ጥበቃ ረገድ የተሠሩ ሥራዎች የተራቆቱ መሬቶችን ወደነበሩበት በመመለስና ምርታማነትን በመጨመር የአርሶ አደሩን ተጠቃሚ ማረጋገጥ ችለዋል።

ባለፉት አምስት ዓመታት በአረንጓዴ አሻራ ከተተከሉት እጽዋት ከስልሳ በመቶ በላይ አርሶ አደሩ መሬት አካባቢ የተተከሉና ለምግብነትና ለእንስሳት መኖነት የሚውሉ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ያላቸው ናቸው ሲሉም አብራርተዋል።

በተጨማሪ ከኢትዮጵያ ተራራማ አካባቢዎች የሚፈልቁ ወንዞች በደን መጠበቅ መጠናቸው ስለሚጨምርና ስለማይቋረጡ ለአርሶ አደሮች፤ ለከተማ ነዋሪችና ለጎረቤት ሀገራት የኢኮኖሚ ምንጭ በመሆን እያገለግሉ ይገኛል ብለዋል።

የደን ሽፋንን ለማሳደግ የሚከናወኑ ሥራዎች ከኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታቸው ባለፈ ለከተሞች የውሃ አቅርቦት፤ ለቱሪዝም ዕድገትና ዓለምን እየፈተነ ላለው የአየር ብክለት ለመቀነስ ትልቅ ፋይዳ አላቸው ነው ያሉት።

የደን ጥበቃና ልማት ሥራዎች መከናወን ያለባቸውም አርሶ አደሩ የባለቤትነት ስሜት እንዲፈጠርበት በማሳተፍ ነው ያሉት ዶክተር ሞቱማ፤ በአሁኑ ወቅትም እንደ ሀገር ማህበረሰቡን በማሳተፍ በርካታ የደን ጥበቃ ሥራዎች እየተከናወኑ መሆናቸውን አንስተዋል።

በቀጣይም የደን ልማቱ ገቢ ሊያስገኝና አርሶ አደሩንም በዘላቂነት ተጠቃሚ የሚያደርግ እንዲሆን የሚሰራ መሆኑን ጠቁመዋል።

የግብርና ሚኒስትር ዴኤታ ፕሮፌሰር እያሱ ኤልያስ በበኩላቸው፤ ደን የአፈር መሸርሸርን በመከላከል



ሞቱማ ቶሌራ (ዶ/ር)

የመሬት ለምነት እንዲጠበቅ እና የአየር ንብረት ለውጥ እንዲቀንስ በማድረግ ለአርሶ አደሩ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል ብለዋል።

ነገር ግን በኢትዮጵያ እስከ ቅርብ ጊዜ በዓመት 100 ሺህ ሄክታር የሚደርስ ደን ይጨፈጨፍና በሰደድ እሳት ይወድም ነበር ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ይህንንም ተከትሎ የአካባቢ መራቆት፣ በርሃማነትና ድርቅ እየተከሰተ በርካታ ዜጎች ለምግብ እጥረትና ለድህነት ሲዳረጉ ቆይተዋል ብለዋል።

በአሁኑ ወቅት ግን ይህ የደን ጭፍጨፋና ቃጠሎ ለመከላከል በተሰሩ የደን ልማትና ጥበቃ ሥራዎች ሽፋን 32 ሺህ ሄክታር ማድረስ በመቻሉ በየዓመቱ ምርትና ምርታማነት እየጨመረ ይገኛል ሲሉ አስረድተዋል።

የደን ልማቱ ለንብ ማነብና ለወተት ምርት ብሎም ለአጠቃላይ የሥርዓተ ምግብ ለውጥ ትልቅ አስተዋጽኦ እያበረከተ እንደሚገኝም አያይዘው ገልጸዋል።

በአፍሪካ በሁለተኛ ደረጃ እየላክን ያለነውን የአቦካዶ ምርትን ጨምሮ ሌሎች ፍራፍሬዎችም የምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ አልፎ ለውጪ ምንዛሬም ማግኛ እየሆኑ መምጣታቸው በደን ልማት ረገድ የተሠሩ ሥራዎች አበረታች ውጤት እያስመዘገቡ መሆኑን አመላካች ነው ብለዋል።

# “የኢትዮጵያ ምልዑነት ሊረጋገጥ የሚችለው ሁሉም እምነት፣ ባህልና ታሪክ በልክ ሲቀመጡ ነው”

## - ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ምልዑነት ሊረጋገጥ የሚችለው ሁሉም እምነት፣ ባህልና ታሪክ በልክ ሲቀመጡ ነው ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ገለጹ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ከተለያዩ አካባቢዎች ከተውጣጡ የሃይማኖት አባቶች ጋር ሰሞኑን ተወያይተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሲኖዶስና ከተለያዩ አካባቢዎች ከተውጣጡ የሃይማኖት አባቶች ጋር ባደረጉት ውይይት እንደገለጹት፤ መንግሥት ሁሉም ማህበራዊ እሴቶች የሀገር ህልውና መሰረት በመሆናቸው መጠናከር አለባቸው ብሎ ያምናል።

የኢትዮጵያ ምልዑነት ሊረጋገጥ የሚችለው ሁሉም እምነት፣ ባህልና ታሪክ በልክ ሲቀመጥ መሆኑን ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገልጸዋል።

ኦርቶዶክስን በሚመለከት ምንም የተናወጠ አቋም የለኝም ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ለኢትዮጵያ መሠረት፣ ጽኑ ምሰሶና የማይፈርስ አስፈላጊ ተቋም ነው ሲሉ አብራርተዋል።

ክርስትና፣ እስልምና፣ ቅዳሴና አዛን የኢትዮጵያ መገለጫዎች መሆናቸውንም አንስተዋል።

እኛ የምንፈልገው እምነትም መንግሥትም በራሳቸው ሕግ፣ ሥርዓትና መርህ እንዲመሩ፤ እንዲሁም አንዱ ለአንዱ ጋሻ በመሆኑ አስፈላጊ በሚሆኑ ጉዳዮች ላይ አብረው እንዲሠሩ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ የእምነት ተቋማትን በሚመለከት በቅርቡ አዋጅ ስለሚወጣ የእምነት ተቋማት በአዋጁ ላይ በመወያየት ሃሳባቸውን ሊያስቀምጡ እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

ሀገር የማስተዳደሩ ሥራ መቶ በመቶ የመንግሥት ሥራ መሆኑን የገለጹት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፤ ወንጌል እንዴት ይስፋፋል የሚለው ደግሞ የሃይማኖት አባቶች ሥራ መሆኑን አብራርተዋል። በዚህም መሠረት መተጋገዙ ተገቢ ቢሆንም አንዱ በሌላው ጣልቃ ሳይገባ መሥራት የሚገባው መሆኑን ተናግረዋል።

ወንጌል የሚስፋፋው ሀገር ለመጠበቅ፣ ትውልድ ለማነጽ፣ የሰላምን አውድ ለመፍጠር በሚችል መልኩ መሆኑን ጠቅሰው፤ በመሰል ጉዳዮች ላይ መንግሥት እገዛ ሊያደርግልን ይገባል ብሎ ጥያቄ ማቅረብ አግባብ መሆኑን አስረድተዋል።

ባለፉት አምስት ዓመታት እምነትና መንግሥት ነጻና ገለልተኛ ሆነው እንዲሠሩ፣ ሕጋዊ እውቅና እንዲያገኙ፣ ችግሮች ሲያጋጥሙ በውይይት እንዲፈቱ ተደርጓል ብለዋል።

ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት በአዲስ አበባ ብቻ የአምልኮ ቦታ 68፣ ለታቦታት ማደሪያ 40፣ ለመንበረ ጵጵስና አንድ፣ ለማዕከል ሁለት በጥቅሉ 111 ቦታዎች ከአንድ ነጥብ አንድ ሚሊዮን ካሬ መሬት በላይ መሰጠቱን አስታውቀዋል።

ቋንቋና ባህልን በሚመለከት ለመስፋፋት በሚያስችል መልኩ መሥራት እንደሚገባ ገልጸው፤ ቋንቋን በሚመለከት ቅሬታ ስታዩ በመወያየትና በንግግር መፍታት ይገባል ብለዋል።

ከኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት አመራሮችና ከተለያዩ ክልሎች ከተውጣጡ አባቶች ጋር ባደረጉት ውይይት፤ በ1966 ዓ.ም ሙስሊሞች 13 ጥያቄዎችን የያዘ ከፍተኛ ንቅንቄ ሲያደርጉ እንደነበር አስታውሰዋል።

በኢትዮጵያ መንግሥት በሚቀያየርበት ዘመን የሙስሊሞች እንቅስቃሴና ጥያቄ እንደነበርም አንስተዋል።

የሙስሊም ሕጋዊ እውቅና ማግኘት፤ የመደራጀት መብት፤ የመስጊድ ግንባታ ፈቃድ እንዲሁም ሸሪዓን በተመለከተ በርካታ ጥያቄዎች ሲነሱ እንደነበር ያስታወሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ከሚነሱት ጥያቄዎች የተመለሱ ቢኖሩም አሁንም ብዙ ይቀራል ሲሉ አብራርተዋል።

ኢትዮጵያ የሙስሊሙም የክርስቲያኑም ሀገር በመሆኗ በተለይ ሙስሊም ወጣቶች እኛ ሁለተኛ ዜጋ ነን እየተገፋን ነው የሚለውን እሳቤ ሊያስተካክሉ እንደሚገባ ገልጸው፤ በሀገራቸው ከሌሎች ወንድሞች ጋር በእኩል የመኖርና የመጠየቅ መብት እንዳላቸው ገልጸዋል።

ባለፉት አራትና አምስት ዓመታት በአዲስ አበባ 124 ቦታዎች ለመስጂድ መሥሪያ፣ ሦስት የቀብር ቦታ፣ ለማዕከል አንድ ቦታ መሰጠቱን ገልጸው፤ ኢትዮጵያ አቅም በፈቀደ መልኩ የእምነት ተቋማትን ጥያቄ ለመመለስ ወደፊትም በተጠናከረ ሁኔታ ይሠራል ብለዋል።

የወሰዱትን ቦታ አጥረው ያስቀመጡ የእምነት ተቋማት ለታለመለት ዓላማ ሊያውሉት ይገባል ሲሉም ማሳሰቢያ ሰጥተዋል።

ኢስላሚክ ዩኒቨርሲቲ፣ ኢስላሚክ ትምህርት እና አረብኛ ቋንቋን ለመጀመር እውቅና ይሰጠን የተባለውን ጥያቄ አስመልክተውም፤ ለሌሎች የእምነት ተቋማትም እውቅና ለመስጠት አቅጣጫ የተቀመጠ ስለሆነ ጥናት ተጠንቶ በጋራ ይመለሳል ብለዋል።

አረብኛ ቋንቋ ትምህርት ለሚለው ግን ኢትዮጵያውያን አረብኛ ቋንቋ አለማወቃችን ጉዳት በመሆኑ ለቢዝነስ ዲፕሎማሲ ሲባል ቢጠናከር ጥሩ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

በመንግሥት ትምህርት ቤቶች የአለባበስ ሥርዓትን በተመለከተ ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመመሪያው ዙሪያ እንነጋገራለን ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በእኔ በኩል ግን በትምህርት ቤት አካባቢ ሲቪክ የሆነ አቀራረብ ቢኖር መልካም ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ እንዳሉት፤ ኢትዮጵያ የዓለም አቀፍ ተቋማት አባል አለመሆኗ ጉዳት አድርሶባታል። በአረብ ሊግ የአባልነት እንኳን ባይሆን የታዛቢነት ወንበር ባለማግኘታችን ስለኢትዮጵያ የፈለጉትን እንዲናገሩ ፈቅደናል። የታዛቢነት ወንበር ማግኘት ጠቃሚ በመሆኑ የኢትዮጵያ ሙስሊምና መንግሥት በትብብር ልንሠራባቸው ይገባል።

በአፋርና በሶማሌ ክልሎች አስተማማኝ ሰላም እንዲኖር የተጀመረው ጥረት የሚበረታታ መሆኑን ገልጸው፤ ለስኬታማነቱ መንግሥት አስፈላጊውን ድጋፍ እንደሚያደርግ አስታውቀዋል።

ከአፍሪካና ሌሎች ሀገራት ጋር ከሀገሪቱ እምነት፣ ባህልና እሴት የሚጣረሱ ስምምነቶች ተፈራርመዋል ለተባለውም ለኢትዮጵያ የማይመች አንቀጽ ካለው አይፈጸምም ብለዋል።

ከኢትዮጵያ ወንጌላዊያን አብያተክርስቲያናት ካውንስልና አባል አብያተክርስቲያናት ተወካዮች ጋር ባደረጉት ውይይት፤ ፕሮቴስታንቶች እንደዜጋ የቀብርና የማምለኪያ ቦታ ማግኘት ይገባቸዋል ብለዋል።

ጥያቄአቸው እስካሁን በተወሰነ ደረጃ የተመለሰ ሲሆን፤ ወደፊት ደረጃ በደረጃ ሁሉንም የማስተናገድ ሥራ የሚሠራ መሆኑን ገልጸው፤ የተጀመሩትን ሥራዎች ለማጠናቀቅ መተጋገዝ ወሳኝ ነው ብለዋል።

በኢትዮጵያ ጴንጤ፣ ፕሮቴስታንትና ወንጌላውያን የሚገባችሁን ቦታ አግኝታችኋል ወይ ከተባለ ቢበዛ ሁለት በመቶ ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ቤተ አምልኮ ግንባታን በተመለከተ የተነሱ ችግሮችን ከሌሎች ሃይማኖቶች ልምድ በመውሰድ መፍታት እንደሚቻል ጠቁመዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ አሁን ያለው መንግሥት የፕሮቴስታንት ሳይሆን የኢትዮጵያ መንግሥት በመሆኑ የተለየ ባለቤት ለመሆንና ደጋፊ ለመሆን አትሞክሩ ብለዋል።

ይሄንን እውነት ከዘነጋን ከመቀራረብ ይልቅ መራራቅን እናስፋፋለን ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ለመከፋፈል ፍላጎት ያላቸው ሰዎች በሰከነ መንፈስ በመወያየት ጠንካራ ተቋም በመገንባት ለኢትዮጵያ ኩራት መሆን እንደሚገባ ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ ውስጥ ሰላምና አንድነትን ማረጋገጥ ብንችል የከፋት ሃሳብ ያላቸው ሰዎች ሀገር ለመውረር እንደማይነሳሱ ገልጸው፤ መንግሥት ካለው የሰላም ፍላጎት የተነሳ እስረኛ መፍታቱን፣ በውጭ ሀገር የሚኖሩ ዜጎችን ወደሀገር ውስጥ ማስገባቱን እና ለተፎካካሪ ፓርቲ አባላት ስልጣን ማጋራቱን ተናግረዋል።

አንዳንድ ሰዎች በራሳቸው እሳቤና መመዘኛ ለእነርሱ ሰላም ብለው የሚያስቡት አሁን ያለው መንግሥት ከሌለ ብቻ መሆኑን ጠቁመው፤ ሰላም ሊፈጠር የሚችለው ልዩነትን ማክበር እና አብሮ የመኖር ሥርዓትን ማዳበር ሲቻል መሆኑን አስገንዝበዋል።

# “የኢትዮጵያን ታላቅነት ጠብቆ ለትውልድ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ሠራዊት መገንባት ተችሏል።

ከለውጡ በኋላ የኢትዮጵያ ወታደራዊ ተቋማት ላይ የቴክኖሎጂ፣ የመሠረተ ልማት እና የሥርዓተ ትምህርት ማሻሻያ ተደርጓል ያሉት ጠቅላይ ኢታማዦር ሹሙ፤ አሁን ላይ የኢትዮጵያን ታላቅነት ጠብቆ ለትውልድ ማስተላለፍ የሚችል የመከላከያ ሠራዊት መገንባቱን ተናግረዋል።

የመከላከያ የሪፎርም ሥራ ከተጀመረ አራት ዓመት እንደሆነውም አያይዘው አንስተዋል።

እንደ ሀገር የተሰጠውን ኃላፊነት በብቃት የሚወጣ ሠራዊት መገንባት ላይ በትኩረት የተሠራ መሆኑን የገለጹት ጠቅላይ ኢታማዦር ሹሙ፤ መከላከያ ሠራዊት የእውቀት፣ የሙያና የቴክኖሎጂ ምንጭ እንዲሆን በርካታ ሥራዎችን መሥራት ያስፈልጋል ብለዋል።

እንደ ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ ገለጻ፤ በ2025 የኢፌዴሪ መከላከያ ዋር ኮሌጅ ከአፍሪካ ቀዳሚው የስትራቴጂክ አመራር ማሰልጠኛ እንዲሆን በትኩረት እየተሠራ ነው።

ከኮሌጁ ተመርቀው የሚወጡ ሰልጣኞች ሠራዊቱን በአስተሳሰብ፣ በእውቀትና በጥበብ መምራት የሚችሉ መሆናቸውን ጠቁመው፤ ከዚህም ባለፈ የሀገሪቱን ነባራዊ ሁኔታ ለሌሎች ማስረዳት የሚችሉ እና የሀገሪቱን ሉዓላዊነቷን ማስጠበቅ የሚችሉ ናቸው ሲሉ ተናግረዋል።

ለምርቃት የበቁ የሠራዊቱ አመራሮች የጨበጡትን እውቀት በአግባቡ ተግባራዊ በማድረግ የኢትዮጵያን ብሄራዊ ጥቅም የማስከበር ሚናቸውን ሊወጡ ይገባል ብለዋል።

የመከላከያ ዋር ኮሌጅ ዋና አዛዥ ብርጋዴር ጄኔራል ቡልቲ ታደሰ በበኩላቸው፤ ኮሌጁ በመደበኛ አጭር ኮርስ ስልጠና ጄነራል መኮንኖች እና ከፍተኛ መኮንኖችን አሰልጥኖ አስመርቋል። ምረቃው ኮሌጁ ተልዕኮውን በብቃት እየተወጣ ለመሆኑ ማሳያ ነው ብለዋል።

ተመራቂዎች በቆይታቸው ባገኙት ዕውቀት ሌሎች መኮንኖችን ለማፍራት መትጋትና የዕለት ተዕለት ሥራዎቻቸውን በብቃት መወጣት እንዳለባቸው አሳስበዋል።

የሠራዊቱን አቅም የሚያሳድጉ ኮሌጆች፣ የትምህርትና ስልጠና ማዕከላትን የማጠናከር ሥራው ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።

በምረቃ ሥነ ሥርዓቱ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የውጭ ግንኙነትና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ዶክተር ዲማ ነገዎ፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር ብርቱካን አያኖ፣ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የአፍሪካ ጉዳዮች ዳይሬክተር ጄኔራል አምባሳደር ፍስሃ ሻውል ተገኝተዋል።

# አሳሳቢ እየሆነ የመጣው የድምጽ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ሕዝብ በሚበዛበት አካባቢ ላደረጉ ሰዎች እንዲሁም ትምህርት ቤቶችና ሆስፒታሎች ላይ ያለው አሉታዊ ተጽእኖ ከባድ ነው። ይህም ታማሚው ሕመሙን እንዳያስታምም፤ ተማሪውም ትምህርቱን እንዳይከታተል ያደርጋል።

እነዚህ ችግሮች በስፋት ወደሚስተዋልባቸው የከተማዋ አካባቢዎች ምልከታ ያደረገው ኢፕድ የመጀመሪያ ቅኝቱን የአዲስ አበባ ሕዝብ ወደሚበዛበት መገናኛ አካባቢ አድርጓል። ይህ አካባቢ ጭንቀት የሚፈጥር ጫጫታ ያለበት ስፍራ ነው። በዚህ አካባቢ በተለይ በሥራ መውጫና መግቢያ ሰዓት ላይ መገኘት ችግሩን ከባድ ያደርገዋል።

በዚህ ስፍራ ማንኛውም ሰው ገና ከታክሲ እንደወረደ እዚህም እዚያም ከፍተኛ ጫጫታ ይቀበለዋል። ትርምሱን ለማለፍ በሚሄድባቸው የተጨናነቁ መንገዶች ደግሞ የሕገወጥ ነጋዴዎች፣ መንገዶች በሚጨናነቁበት ወቅት አሽከርካሪዎች ያለ ኃላፊነት በሚጠቀሟቸው የመኪና ክላክሶች፣ ከንግድ ቤቶች በሚወጡ ለጆሮ የሚከብዱ ሙዚቃዎች፣ ለልመና ተብሎ በሚከፈቱ ሞንታርቦዎች ጆሮ ይደነቁራል። እሱን አለፈኩ ብሎ ሌላ ታክሲ ለመያዝ ተሰልፎ ባለበትም ከየት መጡ ያልተባሉ የሃይማኖት ሰባኪዎችና የታክሲ ደንብ አስከባሪዎች እንዲሁም ረዳቶች በተራቸው መጮሃቸውን ይቀጥላሉ።

ወይዘሪት መቅደስ ግርማ የሥራ ሁኔታዋ አስገድዷት መገናኛ የምትውል ወጣት ናት፤ በሥራ ቦታዋ ላይም ለማስታወቂያ ያለቅጥ የሚከፈቱ ሞንታርቦዎች፣ የረዳቶች፣ የሕገወጥ ነጋዴዎች፣ የመኪና ክላክሶች በተለይ አሁን አሁን የሃይማኖት ትምህርት የሚያስተምሩ ሰዎች ድምጽ ከአቅም በላይ እንደሆነባት ትናገራለች።

እኔስ እንጀራዬ ስለሆነና ስለለመድኩት ነው እንጂ የሚሰማው ድምጽ በጣም ይረብሻል የምትለው መቅደስ፤ ለሰፈሩ አዲስ የሆነ ሰው ሲመጣ ለትንሽ ደቂቃ እንኳን መቆም እንደማይችል ትናገራለች።

መቅደስ መገናኛ መጥቶ ሳይጨነቅ አለፍ ሲልም በድምጽ ብክለት ሳይበሳጭ የሚያልፍ የለም ስትል ገልጻ፤ ይህን ችግር የሚመለከት ሕግ ካለ መሬት ላይ ቢወርድና ርምጃ ተወስዶ ሁሉም ነገር በልኩ ቢሆን ስትል አስተያየቷን ትሰነዝራለች።

በሥራ ምክንያት ይህን ሰፈር ሳይረግጡ እንደማይውሉ የሚናገሩት ደግሞ አቶ መሐመድ አህመድ ናቸው። መገናኛ ሲደርሱ ቶሎ ከጫጫታው ለመውጣት የተቻላቸውን እንደሚያደርጉ ይገልጻሉ።

በአካባቢው ከፍተኛ የሕዝብ ፍሰት ከመኖሩ ጋር ተያይዞ በየመንገድ ጥጉ ላይ ከተደረደሩት ነጋዴዎች የሚወጡት ድምጽ ብሎም በሞንታርቦ የሚለቀቀው እርዳታና የሃይማኖት ድምጾች ሲጨመሩበት በቦታው ላይ ለደቂቃ መቆየት የማይታሰብ አድርጎታል ይላሉ።

ሌላኛውን ምልከታ በአዲስ ከተማ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አካባቢ ያደረገው ኢፕድ የድምጽ ብክለቱ ለመማር ማስተማር ሂደቱ ፈታኝ እንደሆነ ማስተዋል ችሏል ።

መምህር ዳግማዊ ታፈሰ እንደሚናገሩት፤ አዲስ ከተማ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አስፋልት ዳር መሆኑ ለዚህ ችግር ተጋላጭ አድርጎታል።

በዚህ አካባቢ የመኪና ክላክስን ጨምሮ ሁሉንም አይነት ድምጽ በሚባል ደረጃ በመማሪያ ክፍሎች ድረስ እንደሚዘልቅ ጠቅሰው፤ ይህም የመማር ማስተማር ሂደቱን ለማካሄድ ከባድ አድርጎታል ይላሉ።

መምህር ዳግማዊ፤ በቅርብ እንኳን ከአንድ ስሙን መጥቀስ ካልፈለጉት የመንግሥት ድርጅት በሚወጣ የጄኔሬተር ድምጽ ከተማሪዎቻቸው ጋር መሰማማት ስላልቻሉ ክፍለ ጊዜውን ለማቋረጥ እንደተገደዱ ያስታውሳሉ።

ይህ ችግር አዲስ ከተማ ትምህርት ቤትን ብቻ ሳይሆን በከተማዋ በሚገኙ ብዙ ትምህርት ቤቶች ላይ ይስተዋላል ያሉት መምህሩ፤ የሚመለከተው አካል በተለይም ትምህርት ቤቶች ላይ ትኩረት ሰጥቶ ሊሠራ ይገባል ሲሉ ይናገራሉ።

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ ብክለት ክትትልና ጥናት ዴስክ ኃላፊ አቶ ለሜሳ ሂርጳ በበኩላቸው፤ ባለስልጣኑ የድምጽ ብክለትን ጨምሮ የአየር፣ የመሬት እንዲሁም የውሃ ብክለት ላይ ሰፊ ሥራዎችን ይሠራል።

በአሁኑ ጊዜ የድምጽ ብክለት ላይ ልዩ ትኩረት አድርገው እየሠሩ መሆኑን የገለጹት ኃላፊው፤ በሀገሪቱ በተለይም በአዲስ አበባ ያለው የድምጽ መጠን ከደረጃ በላይ መሆኑን ይጠቁማሉ።

የድምጽ ደረጃ የሚለካው በቀንና በሌሊት ተለይቶ ነው ያሉት አቶ ለሜሳ፤ በዚህም መሠረት ለኢንዱስትሪዎች በቀን 75 በማታ 70 ዴሲሜል ሲሆን፤ ለንግድ አካባቢዎች በቀን 65 በማታ 55 ዴሲሜል መሆኑን ይናገራሉ።

ህብረተሰቡ በሚኖርበት አካባቢም ምንም አይነት ከደረጃ ያለፈ ድምጽ እንዳያስቸግረው በመኖሪያ ቤቶች አካባቢ የተቀመጠው ደረጃ በቀን 55 በማታ 45 ዴሲሜል መሆኑን ያብራራሉ ።

አቶ ለሜሳ ከተቀመጠው የድምጽ ደረጃ በላይ የተጠቀሙ የልማት ድርጅቶችም ሆነ ሌላ አካላት ከጽሁፍ ማስጠንቀቂያ እስከ ገንዘብ ቅጣት የሚያደርስ የህግ ማዕቀፍ እንዳላቸው ገልጸው፤ ከመንግስት እውቅና የሌላቸው አካላት ማለትም በየመንገዱ የተለያዩ ድምጾችን በማሰማት የተለያዩ ተግባራትን የሚፈጽሙ ሰዎችን ከማህበረሰቡ በሚመጣ ጥቆማ ከደንብ አስከባሪዎች ጋር በመሆን ርምጃ የሚወሰድ መሆኑን ይናገራሉ ።

በዋናነት ችግሩን ለመቅረፍ ኅብረተሰቡ ላይ ግንዛቤ መፍጠር ያስፈልጋል ያሉት ኃላፊው፤ ይህንንም በማሰብ በቀጣይ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች ለመሥራት መታቀዱን ተናግረዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ትውልዱ በስክነት እና በአርቆ አሳቢነት የተሻለች ሀገር የመገንባት ኃላፊነቱን መወጣት ይጠበቅበታል!

እያንዳንዱ ትውልድ በታሪክ ፍሰት ውስጥ ዘመኑን /ወቅቱን በገዛው አስተሳሰብ እና አስተሳሰቡ በወለደው ተግባር የራሱ የሆኑ በመጥፎም ሆነ በበጎ የሚጠቀሱ ዐሻራዎችን ጥሎ ያልፋል። ይህ በየትኛውም የዓለም አካባቢ እና ዘመን የሚገኝ ትውልድ የተጓዘበትና እየተጓዘበት ያለ የሕይወት ጎዳና ነው።

በዚህ የሕይወት መንገድ አንዳንድ ትውልዶች፣ ዘመናቸውን በተሻለ መንገድ በመገንዘብ ዘመኑን በሚዋጅ አስተሳሰብ ተገርተው፤ ለራሳቸው፣ ለሀገራቸው፤ ከዚያም አልፈው ለመላው የሰው ልጆች የሚሆኑ በበጎነት የሚጠቀሱ ተግባራትን አከናውነዋል፣ በዚህ ታሪካቸውም ሁሌም ከመቃብር በላይ ቆሞ የሚሄድ ሆኗል።

ሌሎች ደግሞ ባልተገባ መንገድ በተገሩበት የተዛባ አስተሳሰብ፤ በስሜትና በእልህ፣ በራስ ወዳድነትና በማንአለብኝነት፤ በጥላቻና በከፋ ዘረኝነት መንፈስ ተለክፈው ዓለምን የመከራና የስቃይ ፤ የጥፋትና የእልቂት አውድማ አድርገዋት አልፈዋል ፣ በዚህ እኩይ ተግባራቸውም በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ ሁሌም ሲኮነኑ ውለው ያድራሉ።

ዓለም እነዚህን ሁለት ጽንፍ የረገጡ አስተሳሰቦች እና አስተሳሰቦቹ የወለዷቸውን ክፉና ደግ ተግባራት በማስተናገድ ዛሬ ላይ ደርሳለች፤ ከመጣችባቸው ከነዚህ መንገዶች በመማር የሄደችባቸው የመታረም መንገዶችም የአሁኑ ትውልድ የተረጋጋ ሕይወት እንዲመራ መልካም እድል ፈጥሮለታል።

ከዛም በላይ አሁን ላይ ዓለም ለደረሰችበት ማህበራዊ ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያው እድገት፤ የቴክኖሎጂ ልቀትና የአስተሳሰብ ከፍታ ይህ ከትናንት እየተማሩ የመምጣቱ እውነታ ትልቅ ስፍራ እንደሚኖረው ፤ ነገ ላይም ለሚታሰበው የተሻለች ዓለም ግንባታ ከፍ ያለ አቅም እንደሚሆን ይታመናል።

ከትናንት ስህተቶች ተምሮ ቢያንስ ቢያንስ ፤ ዛሬዎች የትናንት ስህተቶች ጥላ ሰለባ እንዳይሆኑ ማድረግ፤ የትናንት ስህተቶችን በመድገም ከሚከፈል ያልተፈለገ ዋጋ ራስን መታደግ የአንድ ጤነኛ ትውልድ መገለጫ ፤ ዋነኛ ኃላፊነት ነው። ራስን ሆኖ የማለፍ ተፈጥሯዊ ማንነቱ መገለጫ ጭምር ነው።

ይህንን እውነታ በአግባቡ አለማጤን ፤ ቆም ብሎ ከትናንት ክፉና ደግ ታሪኮች ተገቢውን አስተምሮ ለመውሰድ የተከፈተ ልብ እና አእምሮ የማጣት እውነታ እንደ ሀገር እኛ ኢትዮጵያውያንን ብዙ ያልተገባ ዋጋ እንድንከፍል እያስገደደን ያለ እውነታ ነው። ችግሩ ዛሬ ላይ በብዙ ተስፋ የጀመርነው የለውጥ ጉዞ ሳይቀር በፈተናዎች እንዲንገጫገጭ አድርጎታል።

በርግጥ እኛ ኢትዮጵያውያን ካለን የረጅም ዘመን የሀገረ መንግሥት ግንባታ አኳያ ፤ ዛሬዎቻችንን በተሻለ መንገድ መምራት የሚያስችሉ ሰፊ ተሞክሮዎች/ታሪኮች ባለቤት ነን። እንደ ሀገር ስለ ነፃነት፣ ፍትህ የከፈልናቸው ዋጋዎችና ያጎናጸፉን ልዕልና ከእኛ አልፎ በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ያተረፉልን ናቸው።

ከእነዚህ እውቅናዎች በስተጀርባ ያሉ መንፈሳዊ፣ ማህበራዊና ባሕላዊ እሴቶቻችንን ለይተን፣ ለዛሬ ብሔራዊ ማንነታችን ግንባታ አቅም አድርገን በመጠቀም አለመቻላችን፤ ከዛም በላይ እንደ ሀገር ካለንበት የግጭት አዙሪት የዳረጉንን የተዛቡ እሳቤዎች እና ምንጮቻቸውን ቆም ብለን ለማየት ፈቃደኝነት ማጣታችን በትናንት ችግሮቻችን ዛሬ ላይ እንድንዳክር አድርገውናል።

ትናንት ላይ በብዙ ምጥ የጀመርናቸው የለውጥ መነሳሳቶች የየትውልዱን ስክነት አጥተው ፤ ከተስፋ መፈክሮች ሳይዘሉ፤ የቁም ቅዠት ያህል ተጨናግፈው ሲቀሩ፤ ለለውጥ የሚከፈሉ መስዋዕትነቶች ሳይቀሩ የታሪካችን ጥቁር ድሪቶ ሆነው፤ ዛሬዎቻችን እየተናጠቁን ዘመናትን ለመቁጠር ተገደናል።

በተለይም በኃይልና በሴራ ላይ የተገነባው የፖለቲካ እሳቤያችን በየዘመኑ የሚገራው ትውልድ አጥቶ፣ እንደ ሀገር እስከ ዛሬዋ ቀን ድረስ ፣ በግጭት አዙሪት ውስጥ እንድንዳክር አድርጎናል። በዚህም ተፈጥሮ የቸረችንን ሀብት ሳይቀር አውቀን በመገልገል፤ ካለንበት ድህነትና ኋላቀርነት መገላገል የሚያስችለንን ዕድል መጠቀም ሳንችል ቀርተናል።

ከዚህ ይልቅ ታሪካዊ ጠላቶቻችንን ጨምሮ በየወቅቱ መነሳታችን የሚያሳስባቸው የውጭ ኃይሎች እኩይ ዓላማ ተጋላጭ አድርገውናል፤ እርስ በርሳችን ላልተገባ መገፋፋት ዳርገውናል፣ የብዙ ጥቁር ታሪኮች ትርክት ባለቤት በማድረግ አንገታችንን አስደፍተውናል። በታሪክ ስብራቶች እንድናነክስ አስገድደውናል።

ይህ ከትናንት ያለመማር ፣ ለዚህ የሚሆን ስክነት የማጣታችን እውነታ ዛሬም በብዙ ተስፋና እልህ የጀመርነውን ለውጥ እየተፍታታ ይገኛል። ባለፉት ትናንቶች በሴራና በኃይል /በእንሞካከር ከመከኑ ትላልቅ የለውጥ ተስፋዎቻችን መማር አለመቻላችን የጀመርነው ለውጥ ፍሬ አፍርቶ ለመጪዎቹ ትውልዶች የመነሳት ጅማሪ እንዲሆን፤ ከሁሉም በላይ ስክነት ፤ እንደ ጤናማ ትውልድ ከትናንት ስህተቶቻችን መማር የሚያስችል የልብና የአእምሮ ዝግጁነት ያስፈልገናል። ዘመኑን የሚመጥን የሚዋጅ የአስተሳሰብ መሠረት መጣልም ይጠበቅብናል።

ችግሮቻችንን በአግባቡ ተረድተን፤ ሁላችንም በንግግር እና በውይይት የመፍትሔ አካል የምንሆንበት አዲስ የአስተሳሰብ ጅማሪ ውስጥ መግባት አለብን። በችግሮች ዙሪያ ጣት ከመቀሰር ወጥተን፤ ከችግሮች ይልቅ ለመፍትሔዎች ትኩረት የምናደርግበትን የትውልድ የአእምሮ ውቅር መፍጠር ይኖርብናል።

ከዚህ ውጭ በየትኛውም መንገድ እና መልኩ ፍላጎቶችን በሴራ እና በኃይል በሀገር እና በሕዝብ ላይ ለመጫን፤ በሁከት እና በጠመንጃ የመንግስት ስልጣን ለመያዝ የሚደረጉ ጥረቶች ከጥፋት ውጪ የሚያመጡት ትርፍ አይኖርም። ይህ ደግሞ ለታሪካዊ ጠላቶቻችን እና በየወቅቱ መነሳታችን ለሚያሳስባቸው የውጭ ኃይሎች እኩይ አላማ ተጋላጭ ከማድረግ ያለፈ ፋይዳ አይኖረውም።

ትውልዱ ይህንን እውነታ ከትናንት ተጨባጭ ታሪኮቹ በአግባቡ በመረዳት፤ እራሱን ከጥፋት መንገድ መቆጠብ፤ ነገሮችን በሰከነ መንገድ ፤ በአርቆ አሳቢነት እና በኃላፊነት መንፈስ ሊመለከት ይገባል። ይህንን በማድረግ ሀገርን እንደ ሀገር ከማስቀጠል ባለፈ የተሻለች ሀገር የመገንባት ኃላፊነቱን መወጣት ይጠበቅበታል!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የመናኸሪያዎቻችን መፀዳጃ ቤቶች

ግርማ መንግሥቴ

መናኸሪያ ሥራው ያው እንደ ስሙ ነው። ዘር፣ ቀለም፣ ፆታ፣ እድሜ ወዘተ ሳይለይ፤ ሁሉንም እኩል የሚያስተናግድ፤ እጅግ ሥራ የሚበዛበት ተቋም ቢኖር መናኸሪያ እንጂ ሌላ ሊሆን አይችልም። በመሆኑም፣ ሁሉንም እኩል እንዲያስተናግድ በርካታ ጉዳዮች ይሟሉለት ዘንድ ግድ ይለዋል።

ልዩ ልዩ የሰውና የተሽከርካሪ ዓይነቶች በዓይነት በዓይነት የሚገኙበት መናኸሪያ በንግድ ሥፍራነትም ሆነ በምንተፋ ጠለፋነት ተወዳዳሪ የለውም የሚሉ በርካቶች ናቸው። ምንም እንኳን ሥፍራው በፀጥታ ኃይሎች ጥብቅና ቅርብ ክትትል የሚካሄድበት ነው ቢባልም፤ በጥብቅና ቅርብ ክትትል ስር እንዳለ አንድ ተቋም ሰላም የሰፈነበት ላለመሆኑ ምስክሮቹ ደንበኞቹ ናቸው።

ተዘረፍኩ፣ ተነጠቅሁ፣ እቃዬን መጫንም ሆነ ማስጫን፤ ማውረድም ሆነ ማስወረድ አልቻልኩም፣ ተሰደብኩ፣ ተገፈተርኩ ወዘተርፈ ብቻ ሳይሆን "መፀዳጃ ሥፍራ አጣሁ" እና የመሳሰሉት የዘወትር ጩኸት የሆኑበት የሀገራችን መናኸሪያ እንደ ሕዝብ መናኸሪያነቱ አረፍ ይባልበት ዘንድ ካፌ እንኳን የለውም። ምናልባት በአዲስ መልክ እየተገነባ ባለው፣ ከቃሊቲው መናኸሪያ እናይ እንደሆነ እንጂ፤ ከነባሮቹ የዚህን ዓይነት አገልግሎት መጠበቅ ማርን ከንቧ ሳይሆን ንብ ካልሆነችው እንደ መጠበቅ ይቆጠራል።

ይህን ስንል እንደ ደብረዘይቷ መናኸሪያ ዓይነት መዝናኛና መፀዳጃን (ከጀርባ ያለው ሳይሆን መግቢያው አካባቢ በስተቀኝ ያለችው) የያዙና ከውጭ ድርጅቶች ጋር በትብብር የተሰሩ እዚህም እዛም ሊኖሩ ይችላሉ። እንደዚህ ፀሐፊ ልምድ ከሆነ ግን "አሉ" በሚባሉበት ደረጃ ላይ ያሉ አይደሉምና አስተያየታችንን ከመቀጠል የሚያስተጓጉሉ አይሆኑም።

እርግጥ ነው፣ አንዳንድ መናኸሪያዎች ሆን ተብለው ሥርዓት አልበኝነት እንዲሰፍን ለሥርዓት አልበኞች ሁነኛ ሥፍራዎችን ያመቻቹ እስኪመስሉ ድረስ ሥርዓት አልበኝነት ሲንሰራፋባቸው ይታያሉ። ብዙዎቹ ሰዎች እንዳይከበሩና እንዳይከባበሩ ሆን ተብሎ እየተሰራባቸው ያሉ እስኪመስል ድረስ ተግባራቱ ሲፈፀሙ ይታያሉ። አስተዳዳሪና ባለቤቱ መንገድ ትራንስፖርት ልክ እንደ ሌሎች ሚኒስትሪዎች ሁሉ ለምን በእነዚህ አካባቢዎች ሥርዓትን እንደማያስከብር ግልጽ አደለም።

በግልጽ እንደሚታወቀው መናኸሪያዎች በትራንስፖርት ሚኒስቴር ስር ናቸው። አስተዳዳሪያቸው እሱ ነው ማለት ነው። ታዲያ ለምን እንደ አንድ በሚኒስትር እንደሚመራ ግዙፍ ተቋም ዘመናዊነት አይስተዋልበትም፤ አሠራር አይዘረጋለትም፤ መዋቅር አይደራጅለትም በመዋቅር አይመራም? ይህ የሁሉም ጥያቄ ነውና ጊዜ መልስ እስኪሰጠው ድረስ መጠበቅ ግድ ይሆናል።

> **መናኸሪያዎች በትራንስፖርት ሚኒስቴር ስር ናቸው። አስተዳዳሪያቸው እሱ ነው ማለት ነው። ታዲያ ለምን እንደ አንድ በሚኒስትር እንደሚመራ ግዙፍ ተቋም ዘመናዊነት አይስተዋልበትም፤ አሠራር አይዘረጋለትም፤ መዋቅር አይደራጅለትም በመዋቅር አይመራም**

ይህ ዘመናትን ያስቆጠረው የመናኸሪያዎች አገልግሎትና ኋላቀርነት ከሰላምና ደህንነት፣ ጤና፣ ሥነ ምግባር፤ ዝርፍያና ቀማኛነት እና መሰል ጉዳዮች አኳያ ሲታይ ያለ መሻሻሉ ምክንያት ምን እንደሆነ እዚህ መልስ ለመስጠት ቢያስቸግርም፣ መልሱን የሚመለከታቸው አካላት አሳምረው ያውቁታልና ወደፊት ይነግሩናል፤ አሠራሩንም ያዘምኑታል ተብለው ይጠበቃሉ።

በመሠረቱ፣ ከላይ እንዳልነው፣ መናኸሪያዎች አካታች እንደ መሆናቸው መጠን ለሁሉም እኩል አገልግሎትን ይሰጡ ዘንድ ይጠበቃሉ። ያ ማለት በርካታ አገልግሎት መስጫ ሥፍራዎችንና ሙያዎችን ይዘው መገኘት አለባቸው፤ ሰላምና ፀጥታ፣ ማረፊያ ክበብ፣ ንፁህ ውሃ፣ ሱቆች፤ ከሁሉም በላይ ፅድት ያሉ መፀዳጃ ቤቶች ያስፈልጋሉ ማለት ነው። ይህ ደግሞ የሰዎች መሠረታዊ ሰብዓዊ መብት እንጂ ችሮታ አይደለም።

መቼም ብዙዎቻችን ከቦታ ቦታ ከመዘዋወራችን አኳያ ከበርካታ መናኸሪያዎቻችን ጋር ትውውቅ ያለን መሆኑ ርግጥ ነው። በዛው ልክ ደግሞ ስለ መናኸሪያዎቻችን ገበና ማየትና ማወቃችን ደግሞ ሌላው ርግጥ የሆነ ምልከታችን ይሆናል።

ለምሳሌ ወደ ደቡብ የሀገራችን ክፍል ሄዶ፣ የአዲሱ ክልል (ደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ) አካል በሆነውን የተርጫ ከተማ መናኸሪያ እየሆነ ያለውን የተመለከተ በመናኸሪያዎቻችን ምን ጉድ እየተሠራ እንደሆነ ይመለከታል። ጉዳዩ እንዲህ ነው።

ከተርጫ ከተማ ወደ ሌሎች ከተሞችም ሆነ ሥፍራዎች ለመሄድ የፈለገ ሰው ተርጫ ከተማ መናኸሪያ መድረስ ያለበት ከሌሊቱ 10 ሰዓት ጀምሮ ነው። በቃ፣ ከዛ ሰዓት ጀምሮ ሰው በሰው ላይ ተደራርቦ ዋናው በርና አካባቢው እስኪጨናነቅ ድረስ ወከባ ይሆናል። የመናኸሪያው በር ልክ 12 ሰዓት ላይ ይከፈታል። የሚገርመው ነገር ቀድሞ የሚገባው 10 ሰዓት ላይ የመጣውና በብርድ ሲለበለብ ያነጋው ሳይሆን ለ12 ሩብ ጉዳይ የመጣው ወጠምሻ ነው።

በቃ፣ ልክ ሲከፈት ሁሉንም ገለባብጦ፣ ገፈታትሮ ከፊት ከች ይላል። ይህ ሁሉ ሲሆን የሚመለከተው አካል ያሰማራቸው "የፀጥታ ኃይሎች" በሥፍራው አሉ። በዚህ ግፍትሪያና ግልበጣ ወቅት የሚፈጠረውን የሰብዓዊ መብት ጥሰት ያየ ብቻ እንጂ ሌላ ሰው በፍፁም ሊረዳው አይችልምና እንለፈው። መፀዳጃ ቤቶችንም ከእንደ እነዚህ ዓይነት መናኸሪያዎች መጠበቅ የሚታሰብ አይደለምና እሱንም እንዝለለው።

አንድ ነገር ግን ብሎ ማለፍ ይገባል፤ ሁሉም እንደ አመጣጡ ቢሰለፍና በሰልፉ መሠረት እንዲገባ ቢደረግ ይህ ሁሉ፣ የእነዛ አቅመ ደካሞች፣ ሴቶችና ሕፃናት እንግልት ባልነበረም ነበር። ሌሎች መናኸሪያዎችንም በዚሁ ልክና መልክ ማየት ይቻላል። የጎንዮሽ ታሪኮችን ትተን፤ መፀዳጃ ቤቶች ላይ ብቻ አተኩረን ትንሽ እንጨዋወት።

ወደገጽ 10 ዞሯል

# የስልጤ ብሔረሰብ ባሕላዊ ምግቦች

በኃይሉ አበራ

በሀገራችን በተለያዩ ብሔረሰቦች ዘንድ የሚዘጋጁ ይዘታቸው በፕሮቲን የበለፀጉ ባሕላዊ ምግቦች አሉ። እነዚህ ምግቦች በመደበኛነት (ለእለት ተእለት) እና በልዩ ቀናቶች (በበዓላት፣ በደስታና በሀዘን) የሚዘጋጁ ናቸው። ይሁን እንጂ እነዚህ የምግብ ዓይነቶች በሌላው ብሔረሰብ ባሕላዊ አዘገጃጀት ወቅት በተመሳሳይ የሚገኙበት ሁኔታም በስፋት ይስተዋላል፡፡ ምግቦቹ የብሔረሰቦች ማንነት መገለጫም ናቸው፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ በርካታ ባሕላዊ ምግቦች በሚገባ የተጠኑና አዘገጃጀታቸውም ተሰንዶ የተቀመጠ እንዳልሆነ ባለሙያዎች ይናገራሉ። በዚህ ምክንያት ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፉት ሥርዓተ ትምህርት ተቀርጾላቸው ትውልዱ እንዲያውቃቸውና እንዲማራቸው በማድረግ ሳይሆን በልማድ ነው፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን እነዚህን ሀገራዊ የሆኑ ባሕላዊ ምግቦችን በማጥነት በመደበኛው የአመጋገብ ሥርዓት የማካተት እና ሌሎች ማህበረሰቦችም የማስተዋወቅ እንዲሁም ወደ ዓለም አቀፍ ገበያ የሚገቡበትን ሁኔታ የማመቻቸት እንቅስቃሴዎች ይታያሉ።

ከዚህ አኳያ አንዱ ሊጠቀስ የሚገባው የስልጤ ብሔረሰብ ባሕላዊ ምግቦች፣ አዘገጃጀታቸውና የአመጋገብ ሥርዓታቸው ነው። ብሔረሰቡ በርካታ የራሱ የሆኑ መገለጫዎች ያሉት ሲሆን፣ ከእነዚህ መገለጫዎቹ መካከል ባሕላዊ ምግቦቹ ይጠቀሳሉ፡፡

ከስልጤ ዞን ባህል፣ ቱሪዝምና ስፖርት መመሪያ ያገኘነው መረጃ እንደሚያመለክተው፤ ብሔረሰቡ ከ135 በላይ የምግብና የመጠጥ ዓይነቶች አሉት። መረጃው እንደሚያመለክተው ምግቦቹና መጠጦቹ በሁለት ዘርፍ መድቦ መደበኛና መደበኛ ያልሆኑ ብሎ መመልከት ይቻላል፡፡

መደበኛ ምግቦችና መጠጦች ማለት ዘወትር ጥቅም ላይ የሚውሉትን የሚያቅፍ ነው። ይህም እንደ ቆጮ፣ ቡና፣ ቆሎ፣ ካሽትዬ የመሳሰሉትን ያካትታል። መደበኛ ያልሆኑ ምግቦች የሚባሉት ደግሞ በተለያዩ ሁኔታዎችና ክስተቶች እንዲሁም ወቅቶች ላይ የሚዘጋጁ ምግቦችን ይመለከታል። በዚህ ዘርፍ እንደ አተካኖ፣ ብላንብሎ፣ ሻሜታ፣ ዙብቆ የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ፡፡

ሀገር በቀል ባህላዊ ምግቦችን በመጠበቅ በሀገሪቱ የአመጋገብ ሥርዓት በማካተት ሂደት ሚናውን እየተወጣ የሚገኘው የኢትዮጵያ ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት፣ የሀገሪቱ ብሔረሰቦች መገለጫዎች የሆኑትን ባሕላዊ ምግቦችና የአመጋገብ እሴቶችን ጨምሮ የተለያዩ ጥናቶችን እያደረገ ይገኛል።

ኢንስቲትዩቱ መሰል ጥናቶችን ካደረገ በኋላም ሰነዱን ለዩኒቨርሲቲዎች፣ ለጤና ተቋማት፣ ለግብርና ቢሮዎችና ሌሎች ለሚመለከተው አካላት ያስረክባል። በቅርቡም ከስልጤ ዞን ባህልና ቱሪዝም እና ስፖርት ቢሮ ጋር በመሆን የተለያዩ ብሔረሰቦች ባሕሎች እንዲሁም የቱሪዝም መስህብ ቦታዎች እና ባሕላዊ ምግቦች ላይ ጥናት አድርጎ ለስልጤ ዞን አስተዳደር አስርክቧል።

የኢንስቲትዩቱ የሕዝብ ግንኙነት ዳይሬክተር ወይዘሮ አስቴር ተክሌ እንደሚናገሩት፤ ኢንስቲትዩቱ ከተሰጡት ተልዕኮዎች ጥናትና ምርምር ማድረግ፣ ሥልጠና መስጠት እና ማማከር የሚሉት ይጠቀሳሉ። በዚህም ከክልሎች ጋር በመሆን በባህላዊ የአመጋገብ ሥርዓቶች ላይ ያተኮሩ ጥናቶችን በማድረግ የምግቦቹን ዝርዝርና አዘገጃጀታቸው በምግብ ዝርዝር እንዲካተት እያደረገ ነው።

ኢትዮጵያ የምትታወቅባቸው ባሕላዊ የአመጋገብ ሥርዓቶቿ እንዳሉ ሆነው በየክልሎቹ በሚገኙ ብሔረሰቦች ዘንድም በርካታ ባሕላዊ የምግብ ዓይነቶች፣ አዘጋጃጀቶችና ሥርዓቶች ይገኛሉ። ከተማ ላይ የማይገኙ የምግብ ዓይነቶችንም በባለሙያ በማጥናት በምግብ ዝርዝር መቅረብ እንዲችሉ እየተደረገ መሆኑን ወይዘሮ አስቴር ተናግረዋል። ቀደም ሲልም 16 የሲዳማ ባህላዊ የምግብ ዓይነቶች በምግብ ዝርዝር ውስጥ እንዲቀርቡ በኢንስቲትዩቱ ባለሙያዎች ጥናት መደረጉንም ጠቅሰዋል።

ኢንስቲትዩቱ አሁን ያደረገው ጥናትም በስልጤ እና በሌሎች ብሔረሰቦችም ዘንድ በተወዳጅነቱ የሚታወቀውን “አተካኖ” የሚባለውን ከእንሰት የሚዘጋጅ



የብሔረሰቡ የምግብ ዓይነቶች በቱሪዝም ማሠልጠኛ ኢንስቲትዩት ተጠንተው ሰነዱ ለዞኑ አስተዳደር ተሰጥቷል፣

ባህላዊ ምግብ በዞኑ ባሉ ደረጃቸውን በጠበቁ ሆቴሎች እና በሀገራችን በሚገኙ ሌሎች ሆቴሎች ጭምር አዘጋጅቶ ለማቅረብ የሚያግዝ ነው።

ምግቡ በማዘጋጀት በኩል እውቀቱ ያላቸው እናቶች በባሕላዊ መንገድ ሲያዘጋጁ ኢንስቲትዩቱም በዘመናዊ መንገድ በመመዘን እና በመለካት ምግቡን ማዘጋጀት የሚቻልበትን መንገድ በማሳየት ሰርቶ እያስረከበ ነው። ኢንስቲትዩቱ በስልጤ ማህበረሰብ ዘንድ በዋናነት ከሚታወቁ የምግብ ዓይነቶች መካከል አንዱ የሆነውን “አተካኖ”ን ጨምሮ የተለያዩ የምግብ ዓይነቶችን በማጥናት ለምግብ ‹‹ሜኖ›› ለማቅረብ በሚመች መልኩ ሰርቶ በቅርቡ ወራቤ ከተማ ላይ በተካሄደ ሥነ ሥርዓት ላይ አስረክቧል።

ኢንስቲትዩቱ እነዚህን እና ሌሎች ባህላዊ ሁኔታዎችን በማጥናት ለቱሪስት መስህብ እንዲሆኑ አቅም መፍጠር ላይ ይሰራል። አቅም እንዲፈጠር ደግሞ በመረጃ የተደገፈ ጥናት ስለሚያስፈልግ ይሄንን እየሠራ መሆኑን ወይዘሮ አስቴር አመላከተዋል።

የጥናት ሰነዱን በመጠቀምም ህብረተሰቡ የአመጋገብ ባህሉን እንዲያስተዋውቅ እድል እንደሚሰጥ አስታውቀው፣ ክልሎችም የራሳቸውን እምቅ ሀብት ለማስተዋወቅ እድል ከማግኘታቸውም በላይ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነታቸውንም የሚያሳደ ጉበት መሆኑን ተናግረዋል።

በኢትዮጵያ ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ጁኒየር አሰልጣኝ አቶ ጌታሁን ደሳለኝ እንዳብራሩት፤ ሀገር በቀል የሆኑ የኢትዮጵያ ባሕላዊ የአመጋገብ ሥርዓቶችን በማጥናት ወደ ሰነድ የመቀየር ሥራዎች ይሰራሉ። በባህላዊ የምግብ ዝግጅቶችም ላይ ሰነድ በማዘጋጀት ለትውልድ እንዲተላለፉ ይደረጋሉ። በመቀጠልም በትምህርት ቤቶች በትምህርት አይነትነት እንዲሰጡ የሚያስችል ሥርዓተ ትምህርት ለማዘጋጀትም መረጃዎቹ ግብዓት ይሆናሉ። ከዚህ ባለፈም ኢትዮጵያ የራሷ የሆኑ በርካታ ምግቦች ያሏት በመሆኑ እነዚህ ዝርዝር ላይ ሰፍረው በቀላሉ ወደ ገበያ ለማቅረብ እንደሚሰራ አመላክተዋል።

በጥናቱ መሠረት ዶክመንት ከተዘጋጀላቸው ባህላዊ ምግቦች መካከል የሆነው የስልጤ ባህላዊ አመጋገብ ሥርዓት እና የምግብ ዓይነቶች ወደ 26 ይደርሳሉ። ከነዚህም መካከል አተካኖ፣ ሱልሶ፣ ሎሎሃድ፣ ፊንታፊንቶ ወይም ጨራጨራ፣ ኪልፋን፣ ጎሳ ጎሳ፣ የቆሲ ወይም ያቆቀሲ በሰር፣ የዳፓ ፊናንቾ የሚሉት ይገኙበታል። የዝግጅት ክፍላችን ከብሔረሰቡ ባህላዊ ምግቦች መካከል ጥቂቱን እንደሚከተለው በርዝር ይቃኛቸዋል፡፡

**አተካኖ፡-** ይህ የምግብ ዓይነት ከእንሰት የሚዘጋጅ ባሕላዊ ምግብ ሲሆን፣ በበዓላት ወቅት ከሚቀርቡት ምግቦች አንዱ መሠረታዊው ነው። በባሕላዊ የጋብቻ ሥነ ሥርዓት ወቅት በሚኖሩ የተለያዩ ሥነ ሥርዓቶች ላይ የሚቀርብ ሲሆን፣ በማንኛውም ወቅት ክብር የሚሰጣቸውን እንግዶች ለመቀበል ይቀርባል፡፡

አተካኖ ቀለል ያሉ ተብለው ከሚታወቁት የምግብ ዓይነቶች ሊመደብ ይችላል። ይህ ባህላዊ የምግብ ዓይነት ያለማባያ ሊበሉ ከሚችሉ ምግቦች መካከልም ይካተታል። በአመጋገብ ወቅትም የአፍ እንቅስቃሴን እምብዛም የማይፈልግና እንደ ገንፎ በቀላሉ ተላምጦ ሊዋጥ ይችላል። ሲዘጋጅም በዋናነት ቡላ፣ አይብ ፣ ቅቤ፣ ሚጥሚጣና ጨው በግብዓትነት በመጠቀም ነው። ከአዘገጃጀት ሂደት ቀላልነት ባሻገር አተካኖ በቀላሉ የሚበላና የሚፈጭ እንዲሁም ጤናማ የሆነ ሰውነት እንዲኖር ለማድረግ ጠቃሜታ እንዳለው ተጠቁሟል፡፡

አሠራሩም፤ በቡላው ውስጡ የሚገኘውን እርጥበት እንዲያደርቅና የቡላው ጣዕም ከጥሬነት ወደ በሳልነት እንዲለወጥ እና የበለጠ እንዲፈረፈር ጥሬ ቡላውን በሰፊ ምጣድ ላይ መቁላት የመጀመሪያ ሥራው ይሆናል። በመቀጠልም የተፈረፈረውን ቡላ በተለምዶ ሳይራ ተብሎ በሚጠራ ሰፊ እቃ ላይ እንዲሰባሰብ ይደረጋል፤ ውሃ በላዩ ላይ በማርከፍከፍ ውሃውን ሲመጥ ጨው፣ ኮረሪማ፣ ቅቤ፣ አይብ፣ ሚጥሚጣ በመጨመር በደንብ ይፈረፈራል።

በመጨረሻም አይብ ተደርጎበት ከለሰለሰ በኋላ የመሃሉን ቦታ በደንብ በማጎድጎድ በቦታው ላይ በሥነ-ሥርዓት ተነጥሮ የተዘጋጀ ቅቤ በመጨመር ይዘጋጃል። ይህ ባሕላዊ ምግብ በትኩሱ የሚቀርብ ሲሆን፣ አካልን ለማዳበር እና የተጎዳ አካልን ለመጠገን እንደሚጠቅም ይገለጻል።

በአብዛኛው የሚዘጋጀው እንደ አረፋ በዓል፣ ሠርግ ባሉት ዝግጅቶች ላይ ነው፡፡ ከጨቅላ ሕፃናት በስተቀር ሁሉም ሰው የሚመገበው የስልጤ ባህላዊ ምግብ ሲሆን፣ ለጨቅላ ሕፃናት የማይሰጠው ምግቡን መፍጨት የሚችል አቅም እንደሌላቸው በማመን ነው።

**ሱልሶ፡-** ይህ ባሕላዊ የስልጤ ምግብ በትኩሱ የሚቀርብ ሲሆን፣ ይህ የምግብ ዓይነት አካልን ለማዳበር እና የተጎዳ አካል እንዲጠግን ጠቀሜታ እንዳለው በስልጤ ብሔረሰብ ዘንድ ይታመናል። የአረፋ በዓልን፣ የሠርግ ድግስን ምክንያት በማድረግ ይቀርባል። ጨቅላ ሕፃናት በስተቀር ሁሉም ሰው የሚመገበው የስልጤ ባሕላዊ የምግብ ነው።

**ሎሎሃድ፡-** ሰውነትን የሚጠግን የስልጤ ባሕላዊ ምግብ ሲሆን፣ ይህ የምግብ ዓይነትም ብዙ ጊዜ የሚዘጋጀው የአረፋ በዓልን ፣ የሠርግ ድግስን ምክንያት በማድረግ ነው። ከጨቅላ ሕፃናት በስተቀር ለሁሉም ሰው ይቀርባል። ለጨቅላ ሕፃናት የማይሰጠው ምግቡን መፍጨት የሚችል አቅም እንደሌላቸው በማመን ነው።

**ፊንታፊንቶ ወይም ጨራጨራ፡-** ይህ የምግብ ዓይነት ከሱልሶ፣ ጉመረ ቁሰ፣ አዝማሞጃት ወይም ጎመን እርስ በርስ ሳይቀላቀሉ ለየብቻ ረግተው የሚቀርቡበት ነው፡፡ በአረፋ በዓል፣ በሠርግ ጊዜ ይቀርባል። ይህም ምግብ ከጨቅላ ሕፃናት በስተቀር በሁሉም ሰው ለምግብነት ይውላል፡፡

ኪልፋን፡- በምግቡ ውስጥ ከንጥረ ምግቦች አኳያ ፕሮቲን፣ ቅባቶችና ማዕድናት ይገኙበታል። በመሆኑም አካልን ያዳብራል፣ የተጎዳ አካልን ይጠግናል። የሚዘጋጀውም የአረፋ በዓልን፣ የሠርግ ድግስን ምክንያት በማድረግ ነው። በሁለት ዓይነት መንገድ ይዘጋጃል፡፡ ከሥጋ እና ከጎመን በቅቤ ተለውሶ በቅጠል እየተደረገ በእጅ ይሰጣል።

**ጎሳ ጎሳ፡-** ከተለያዩ የምግብ ዓይነቶች ምግቦች ማለትም ቡላ፣ ቅንጬ፣ ጎመን፣ ሱልሶ፣ አይብ፣ ምስር፣ የአተር ክክ የሚቀርብ ነው፤ ጎሳጎሰ ብዙ ጊዜ በአመትባል እና በሠርግ ጊዜ በሸክላ ለተመጋቢዎች ቀርቦ በባሕላዊ ማንኪያ ወይም ቀርሼ ይበላል።

**የቆሲ /ያቆቀሲ በሰር፡-** አካልን የሚጠግን የስልጤ ባሕላዊ ምግብ ነው። ለተከበሩ ሰዎች ማለትም ለአማች፣ ቤተዘመድ አባላት እና ለሕዝባዊ እና ሃይማኖታዊ በዓል ማለትም ለረመዳን ጾም ፍች ፣ ለሸዋል ጾም ፍች፣ በመውሊድ፣ በዱአ ቦታ ላይ ይቀርባል። ጨቅላ ሕፃናት ሲቀሩ ሁሉም ሰው የሚመገበው የምግብ ዓይነት ነው። ለጨቅላ ሕፃናት የማይሰጠው ምግቡን መፍጨት የሚችል አቅም እንደሌላቸው በማመን ነው።

**የጄሪ አንገብሶ/ ቅቅል ፍሪምባ፡-** ይህ የክብር ምግብ ማህበራዊ ትስስርን ለመፍጠር ከቤተዘመድ እና ጎረቤት ጋር በአንድ ላይ በመሆን በሽማግሌዎች ወይም በሃይማኖት አባቶች ተባርኮ ለቡና ሥነ-ሥርዓት በተሰበሰቡ ሰዎች ለምግብነት ይውላል። ለአማች፣ ለረመዳን ጾም ፍች ፣ ለሸዋል ጾም ፍች፣ በእርድ ቦታ ላይ የሚዘጋጅ፣ በመውሊድ፣ በዱአ ቦታ በተገኘ ጊዜ ሁሉ ፣ በአረፋ በዓል ሰሞን፣ በጾም ፍች ሰሞን፣ በመውሊድ የሚዘጋጅ ሲሆን፣ ሁሉም ሰው የሚመገበው የስልጤ ባሕላዊ የምግብ ዓይነት ነው።

**የጄሪ ፎሰ /ቅቅል ሻኛ ከነ ሳልገኝ፡-** ይህ የምግብ ዓይነትም የክብር ምግብ ተብሎ ይታወቃል፡፡ ማህበራዊ ትስስርን የሚያጠናክር ነው ይባላል። በጦርነት ወቅት ጀብድ ለፈጸሙ የጦር አበጋዞች፣ በታላልቅ ሰዎች ተባርኮ ይሰጣል። ይህ ምግብ ለጦር አበጋዞች ወይም ጀብዱ ለፈጸሙ የሚቀርብ ቢሆንም፣ ሁልጊዜ በታላላቅ ሰዎች ወይም የሃይማኖት አባቶች ተባርኮ የጦር ጀብዱ የፈጸሙትን በማስቀደም በረመዳን ጾም ፍች እና በሸዋል ጾም ፍች ጊዜ ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች ጎረቤትና ቤተዘመድን ጨምሮ እንደየደረጃቸው ተካፋፍሎ የሚሰጥ የስልጤ ባሕላዊ የምግብ ዓይነት ነው።

**ዩንጬቆ ጉገ/በቅቤ የተለወሰ የዶሮ ቅቅል፡-** ለረመዳንና ለሸዋል ኢዶች አንዳንዴም መድኃኒት ለሚጠቀሙ ሰዎች እንዳይጎዱ ተብሎ፣ ይጠግናቸዋል በሚል ታስቦ የሚዘጋጅ ምግብ ነው ። በምግቡ ውስጥ ከንጥረ ምግቦች አኳያ ፕሮቲን፣ ቅባቶችና ማዕድናትን ይገኛሉ። ይህ በመሆኑም አካልን ያዳብራል፣ የተጎዳ አካልን ይጠግናል። የሚዘጋጀውም ለአማች፣ ቤተዘመድ፣ ለረመዳን ጾም ፍች ፣ ለሸዋል ጾም ፍች ነው፤ በእርድ ቦታ ላይም ይዘጋጃል፣ ስብራት የገጠመው ሰው ሲኖር፣ መድኃኒት የሚወስዱ ሲኖሩ ይዘጋጃል። ሁሉም ሰው የሚመገበው የስልጤ ባሕላዊ የምግብ ዓይነት ነው።

የማህበረሰቡ ባሕላዊ መጠጦች፡- የስልጤ ማህበረሰብ ባሕላዊ መጠጦች ከሆኑት መካከል “ኡቡሽቡሽት” የሚባለው ይገኝበታል። ኡቡሽቡሽቱ የስልጤ የባሕል መጠጥ ሲሆን፣ በጾም ጊዜ ጥቅም ላይ ይውላል፡፡ ሻሜት ሌላው የስልጤ የባሕል መጠጥ ሲሆን፣ በሠርግ ጊዜ፣ በደቦ ሥራ፣ ቤት ሥራ፣ እርሻ ሥራ፣ እንሰት ተከላ፣ አጨዳ፣ አውድማ እና የመሳሰሉት የህብረት ሥራዎች ሲኖሩ ሠራተኛውን ለማጠናከር የሚቀርብ መሆኑን የጥናት ሰነዱ አመላክቷል።

የስልጤ ዞን ባሕልና ቱሪዝም መምሪያ መረጃ እንዳመለከተው፤ በስልጤ ማህበረሰብ ዘንድ የተለዩና በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ አገልግሎት ላይ የሚውሉ ከ135 በላይ የምግብ ዓይነቶች ይገኛሉ። ከእነዚህ ምግቦች ውስጥ 18ቱ የምግብ ዓይነቶች በስልጤ ማህበረሰብ ዘንድ ብቻ የተለመዱና የሚዘወተሩ ናቸው። በስልጤ ማህበረሰብ ውስጥ ብቻ ከሚታወቁት የምግብ ዓይነቶች ውስጥ አተካኖን ጨምሮ ቢያንስ ሁለትና ከዚያ በላይ የምግብ ዓይነቶች በሚገባ ታውቀውና ተለምደው በሀገሪቱ በሚገኙ ዋና ዋና ሆቴሎችና ሬስቶራንቶች ውስጥ እንዲሁም በሁሉም የምግብ መገበያ ሥፍራዎች በሚቀርቡ የዘወትር ምግብ ዝርዝሮች እንዲካተቱ እየተሠራ ነው።

ማህበራዊ

# ወጣቶች

## ባሕላችን አብሮ መብላት ብቻ ሳይሆን አብሮ መሥራትም መሆን አለበት

**ክብረአብ በላቸው**

በኢትዮጵያ በዓመቱ ሁለት ሚሊዮን የሚጠጉ ወጣቶች ሥራ ፈላጊ ይሆናሉ፤ ወይም ወደ ሥራ ዓለም ይቀላቀላሉ። ለእነዚህ ከፍተኛ ቁጥር ላላቸው ዜጎች በመንግሥት ወይም በግል ተቋማት እና ድርጅቶች የሥራ ዕድል መፍጠር ባለመቻሉ አብዛኛው ቁጥር ያለው ወጣት ለሥራ አጥነት ይደረጋል። ይህንን ችግር ለመፍታት ደግሞ ሥራ ጠባቂ ከመሆን ይልቅ ሥራ ፈጣሪ ሆኖ መገኘት የሚጠቅም ነው።

ሆኖም በኢትዮጵያ በርካታ ወጣቶች የሥራ ፈጠራ ባለሙያዎች ቢሆኑም የፈጠራ ሃሳባቸውን ወደ ተግባር ለማዋል የመሥሪያ ቦታ እጥረት፣ የብድር አቅርቦት አለመመቻቸት፣ የገበያ ትስስር አለመኖር እና የክህሎት ክፍተቶችና መሰል ችግሮች እንቅፋት ሆነው ሲገጥሟቸው ይስተዋላል። አንድ ሰው የተሳካለት ሥራ ፈጣሪ ወይም ኢንተርፕርነር ለመሆን አዲስና የተለየ የቢዝነስ ሃሳብ ወይም ዘዴ ይዞ ቢነሳም ተግባራዊ ማድረጊያ ገንዘብ ወሳኝ መሆኑ አያጠያይቅም። ሆኖም እነዚህ ሁለቱ ብቻቸውንም ሥራ ፈጣሪው የተሳካለት የቢዝነስ ሰው እንዲሆን አያስችሉትም።


ሥራ ፈጣሪው፣ ስኬትን መቀዳጀት እንዲችል ወይም ጉዞው ወደ ስኬት የሚገሰግስ እንዲሆን፤ ዓይነተኛ የሆኑ የሰብዕና መገለጫዎች ያስፈልጉታል። እንደ ሥራ ፈጣሪ፣ እነዚህ የሰብዕና መገለጫዎች ወይም ጠባዮች ካሉት ሊያዳብረቻው፣ ከሌሊት ደግሞ እንደ አዲስ በውስጡ ኮትኩቶ ሊያሳድገቻው ይገባል።

በዛሬው የወጣቶች ዓምድ በሥራ ፈጠራ ውጤታማ ከሆኑ ሁለት አብሮ አደግ ጓደኞች ጋር ቆይታ አድርገናል። ወጣት ደረጀ ባቢሶና ወጣት ሳሙኤል ተስፋዬ ይባላሉ። ውልደትና ዕድገታቸው በሲዳማ ክልል አለታ ጩኮ ወረዳ ነው። ከልጅነት እስከ እውቀት አንድ ላይ ያደጉት ደረጀና ሳሙኤል ከመጀመሪያ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በትውልድ አካባቢያቸው ተከታትለዋል። ወጣት ደረጀ ከቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ በኤሌክትሪካልና ኮምፒውተር ምህንድስና በመጀመሪያ ዲግሪ ተመርቋል። ወጣት ሳሙኤል ደግሞ ከሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ በኤሌክትሮ መካኒካል ምህንድስና ተመርቋል።

ወጣት ደረጀ ከጓደኛው ጋር በመሆን አዲስ የሥራ ሃሳብ በማመንጨት ወደ ሥራ የገቡበትን አጋጣሚ ሲያስታውስ የከፍተኛ ትምህርታቸውን በሚከታተሉበት ወቅት በዓለም አቀፍ ደረጃ በተከሰተው የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ምክንያት ከዩኒቨርሲቲ ወደ ቤተሰቦቻቸው በተመለሱበት ወቅት በቆዩባቸው ጊዜያት በመኖሪያ አካባቢያቸው ከሚያዩት ነገር በመነሳት ወደ ሥራ እንደገቡ ይናገራል።

በወቅቱ ከእነርሱ ቀደም ብለው ከከፍተኛ የትምህርት ተቋም ተመርቀው በመንግሥት ሥራ ተቀጥረው የሚሰሩ ጓደኞቻቸውን በሚመለከቱበት ወቅት የሚሰሩት ሥራ አጥጋቢ ካለመሆኑ ባሻገር በሚሰሩት ሥራ ደስተኛ እንዳልነበሩ መታዘባቸውን የሚናገረው ደረጀ «ትምህርት ጨርሰን ከወጣን የእኛም ዕጣ ፈንታ ይህ ነው ብለን አሰብን ስለዚህ ምን ማድረግ አለብን የሚለውን በመነጋገር አካባቢው ላይ ምን አለ ሰው ማግኘት የሚፈልገው አገልግሎት ምንድነው የሚለውን ማጥናት ጀመርን» ይላል።

ብዙ ሰው የማስዋብ /የዲኮሬሽን ሥራ ሲፈልግ አገልግሎቱን የሚያገኘው ሀዋሳ ወይም ሌላ ከተማ ሄዶ ነው የሚለው ደረጀ፤ ለምን ይህንን ነገር እዚሁ በመሥራት ለህብረተሰቡ አናቀርብም በሚል ሥራውን እንደጀመሩ ይናገራል። ሥራው ከተማሩት የሙያ ዘርፍ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የሌለው በመሆን በመጀመሪያ አካባቢ በሥራው ውጤታማ



ወጣት ደረጀ ባቢሶ፣

እንሆናለን ወይ በሚል ፍርሃት የነበረባቸው ቢሆንም በእጃቸው በነበረ ላፕቶፕ ኮምፒዩተር ሥራውን በተመለከተ ከተለያዩ ድረ ገጾች ትምህርት በመውሰድ ራሳቸውን በማስተማር ውጤታማ መሆን እንደቻሉ ይገልፃል።

በሥራው ጅምር ወቅት ትርፍ ማግኘትን ከማስቀደም ይልቅ ስለሥራው ማህበረሰቡ ግንዛቤ እንዲኖረው ለማድረግ ከተለያዩ የወዳደቁ ነገሮች የሰሯቸውን የመኖሪያ ቤት ማስማሪያ ዕቃዎች በነፃ በማቅረብ ወደ ሥራው መግባታቸው በእጅጉ እንደጠቀማቸው የሚናገረው ደረጀ፤ በዛው አካባቢ ምርታቸውን ለማሳየት ብሎም ለሽያጭ ለማቅረብ የሚሆን ሱቅ በመክፈት በሙሉ ትኩረታቸው ወደ ሥራ እንደተሰማሩ ይገልፃል።

ይህንን ሥራቸውን የተለያዩ ማህበራዊ ሚዲያና ድረ ገፆችን በመጠቀም ወደ ተለያዩ አካባቢዎች በማስፋፋት የቀጠሉት ሁለቱ ወጣቶች ይህንኑ መነሻ በማድረግ ዛሬ በተለያዩ የግል ሥራዎች ላይ ተሰማርተው በውጤታማነት እንደቀጠሉ ይናገራል።

በአሁኑ ወቅት በእነርሱ ስር በጊዜያዊነት የቀን ሥራ እየሠሩ ገቢ ከሚያገኙ ሰዎች ውጭ በየወሩ ደመወዝ የሚከፈላቸው 14 ወጣቶች የሥራ ዕድል የፈጠሩት ሁለቱ ወጣቶች፤ በዋናነት ሥራቸው የመንግሥትና የግል ተቋማት መሥሪያ ቤቶችን፣ የመኖሪያ ቤቶች ማስዋብ ቢሆንም ከዚህ በተጨማሪ ካፌና ሬስቶራንት በመክፈት እየሠሩ የተሻለ ገቢ እያገኙ እንደሆነ ወጣት ደረጀ ይናገራል።

«ወደዚህ ሥራ የገባነው የሚለው ሃሳብ ብቻ ይዘን ነበር» ወጣቱ፤ በ2013 ዓ.ም ከመንግሥት የፋይናንስ ድጋፍ ለማግኘት ጥረት በሚያደርጉበት ወቅት መንግሥት ለሥራው የሚያስፈልጋቸውን የገንዘብ ብድር በመመቻቸት ትልቅ ድጋፍ እንዲደረገላቸው ይህም ዛሬ ለደረሱበት ስኬት ወሳኝ ሚና እንደተጫወተ በአሁኑ ወቅትም ይበልጥ ሥራውን ለማስፋት በሀዋሳ ከተማ የቦታ ጥያቄ አቅርበው በጎ ምላሽ እንዳገኙ ተናግሯል።

በአሁኑ ወቅት «እያየን» የሚል ስያሜ የተሰጠው የግል ድርጅት መስርተው በተለያየ የሥራ ዘርፍ ተሰማርተው እንደሚገኙ የሚናገረው ወጣት ደረጀ፤ የድርጅቱ የስም መነሻ ምክንያት ሲያስረዳ በኮቪድ 19 ምክንያት ከዩኒቨርሲቲ በመመለስ ከአምስት እስከ ስድስት ወር ቤተሰብ ጋር በመቀመጥ በሚያሳልፉበት ወቅት በወረርሽኙ ምክንያት በቤተሰብና፣ በጓደኞቻቸው ላይ የደረሰውን የኢኮኖሚ ችግር በመመልከት «ይህንን እያየን የመንግሥት ቅጥር መጠበቅ አግባብነት የሌለው በመሆኑ ከዛሬ ጀምሮ አስተማማኝ የኢኮኖሚ አቅም ለመገንባት የራሳችንን ሥራ ፈጥረን መሥራት አማራጭ የሌለው በመሆኑ ‹እያየን› እንንቃ ለማለት ለድርጅታችን ስያሜ ሰጠን» በማለት ያስረዳል።



ወጣት ሳሙኤል ተስፋዬ፣

ድህንነት ለማሸነፍ ብቸኛው መንገድ ጠንክሮ መሥራት ነው፡፡ ነገር ግን አሁንም በማህበረሰቡ ውስጥ ስለሥራ ያለው አመለካከት ትክክለኛ አይደለም የሚለው ወጣት ደረጄ፤ ሥራ ማለት ቢሮ ተቀምጦ የሚሠራ ብቻ አይደለም፤ ያለን ደሃ ሀገርና ሕዝብ ነው፡፡ ይህንን የዘመናችንን ጠላት ለማሸነፍ ደግሞ ሥራን ሰይንቁ መሥራት የውዴታ ግዴታ ነው፤ ኢትዮጵያውያን ያለብንን ድህነት ለማሸነፍ ያለን መንገድ ጠንክሮ መሥራት ብቻ በመሆኑን ይህንኑ በመገንዘብ መረባረብ ይገባናል ይላል።

«በአካባቢያችንም ሆነ እንደ ሀገር ያለን አብሮ የመብላት፣ የመጫወት በሀዘንም በደስታም ያለን አብሮነት የሚያስቀና ነው» የሚለው ወጣት ደረጀ፤ ይህንን ትልቅ እሴት አብሮ ወደ መሥራት በማምጣት መቀየር አለብን የሚል ትልቅ ራዕይ ስላለን ይህንን ሃሳብ በማስተማር ከሀገሪቱ ሕዝብ ከፍተኛውን ቁጥር የሚይዘው ወጣት ጠንክሮ ሰርቶ እራሱንና ሀገሩን መጥቀም እንዲችል ለማድረግ ዕቅድ እንዳላቸው ተናግሯል።

በቅርቡ በሀገር አቀፍ ደረጃ በተካሄደው የከተሞች ፎረም ልምዳቸውን ያከፈሉት ወጣቶቹ፤ በሚሰሩት ሥራ ትርፍ ማግኘትን ብቻ ሳይሆን ማህበረሰቡን የሚጠቅሙ የተለያዩ የበጎ ፈቃድ ሥራዎችን በመሥራት የማህበራዊ ኃላፊነታቸውን እየተወጡ እንደሆነ ተናግሯል።

«ተግዳሮትን እያነሱ ከመደርደር ይልቅ እያንዳንዳችን ከተለወጥን ሀገር የማትለወጥበት ምንም ምክንያት የለም» የምለው ወጣት ደረጀ፤ አንድ ሰው የራሱን ኃላፊነት ወስዶ እራሱን ከለወጠ ይህ ለውጥ እያደገ ወደ ቤተሰብ፣ ማህበረሰብ እየተቀየረ ከድህነት የተላቀቀች ሀገር እንድትኖረን ማድረግ የሚያስችል በመሆኑ፤ የሁሉም ያላሰለሰ ጥረት የግድ እንደሚል ይናገራል።

ወጣት ሳሙኤል በበኩሉ ሲናገር፤ አንድን ነገር ፈጠራ በተሞላበት መልኩ ወይም ከሌላ ሰው በተለየ መልኩ መሥረት ከተቻለ ውጤታማ መሆን ይቻላል፤ የምንሠራው ሥራ አዲስ ነገር ያማከለ ጥራት ያለው መሆን ከቻለ በሰፊ ገበያ ውስጥ ተሰማርቶ አሸናፊ መሆን ከባድ አይደለም። በተለይ የውበት ሥራ ጥራትን በእጅጉ ስለምፈልግ ከምንም በላይ ለጥራት ቅድሚያ መስጠት አስፈላጊ ነው «እኛም ውጤታማ መሆን የቻልነው በዚህ መርህ መጓዝ በመቻላችን ነው፡፡» ይላል።

ኮቪድ 19 በተከሰተበት ወቅት የነበረው ሁኔታ እጅግ አስፈሪ ነበር የሚለው ወጣት ሳሙኤል፤ የደረሰው የኢኮኖሚ ችግር ነገ እንዲህ ዓይነት ነገር ቢከሰት በምን መልኩ ማለፍ እንችላለን የሚል ጥያቄ የሚያስነሳ በመሆኑ፣ በመንግሥት ተቀጥሮ መሥራት ደግሞ የኢኮኖሚ ነፃነትን የሚያረጋግጥ ባለመሆኑ የግድ ወደ የግል ሥራ መሰማራት አማራጭ የሌለው አድርጎ በመውሰድ ዛሬ ውጤታማ መሆን እንደቻሉ ይናገራል።

ያለነው ድህነት ተደግፈን ነው፡፡ ከወደቅን መነሳት የሚከብድ በመሆኑ፤ ነገ ላለመውደቅ ብቸኛው መንገድ ጠንክሮ መሥራት ነው የሚለው ሳሙኤል፤ ሥራ ሲበል የትኛውም ሥራ ክቡር ነው። የሚናቅ ሥራ የለም፡፡ ይህንን በተመለከተ ያለው የብዙዎቻችን አመለካከት ግን የሚያስተዛዝብ ነው፡፡ ይህም እራሳችንንና ሀገራችን ሰቅዞ ከያዛት ድህነት መውጣት እንዳንችል አድርጎናል፡፡ ይህ ደግሞ መቀየር ያለበት አንገብጋቢ ጉዳይ ነው ይላል።

በቅርቡ የተካሄደው የከተሞች ፎረም ሥራቸውን ለማስፋት መልካም አጋጣሚ እንደፈጠረ የሚናገረው ሳሙኤል፤ ከተለያዩ የመንግሥት አካላት ጋር በመነጋገር በተለያዩ ከተሞች ቅርንጫፍ ለመክፈት የሚያስችል ድጋፍ እንዳገኙ፤ ይህም ድርጅታቸውን ከተወለዱበት አካባቢ ውጭ በመክፈት ወደፊት ለያዙት ሀገር አቀፍ ኩባንያ የመሆን ራዕይ መንገድ የሚከፍት አጋጣሚ በመሆኑ ደስተኞች እንደሆኑ ይናገራል።

ወጣት ሳሙኤል እንደሚናገረው፤ በትምህርት፣ ቴክኖሎጂ፣ በግብርና እና በሌሎችም የኢትዮጵያን ዕድገት በሚያሳልጡ ዘርፎች ሁሉ የኢትዮጵያ ወጣቶች በሥራ ፈጠራ ላይ ተሰማርተው እየሠሩ ቢገኙም ያላቸውን ራዕይ ወደ ተግባር ላይ ለመለወጥ በርካታ ተግዳሮቶች ይጋፈጣሉ፤ ስለዚህ ችግሮችን ለመፍታት ሁሉም ባለድርሻ አካላት ጥረት ማድረግ እንዳለባቸው ገልጿል።

«ልንሰማራ ባሰብንበት የሥራ መስክ፣ አስተማማኝ ችሎታ እንዳለን በራሳችን መተማመን ያስፈልገናል" የሚለው ወጣት ሳሙኤል፤ ለራሳችን የሚታየን የችሎታ ክፍተት ካለብን፣ ራሳችንን ከማታለል ይልቅ ችሎታችንን ለማዳበር መነሣት ወይም ሌላ የሚስማማንን የሥራ መስክ መምረጥ ይኖርብናል። ነገር ግን ችሎታው እንዳለ ካወቅን በፍፁም መዘናጋት አይገባንም "ይላል።

ስኬታማ ኢንተርፕረነሮች ከዛሬው እንቅፋት፣ ውጣ ውረድ ወይም ጊዜያዊ ድል ይልቅ የወደፊቱ ጊዜና የሚደርሱበት ከፍታ የሚታያቸው ናቸው የሚለው ወጣት ሳሙኤል፤ ሁልጊዜም ከወራት፣ ከዓመታት በኋላ ሥራችን የት እንደሚደርስ በማሰብ መቃኘት ይኖርብናል፤ ራዕይና ዓላማችንን ስናስብና የወደፊት ግባችንን መላልሰን የምናስብ ስንሆን፣ ዛሬ የሚገጥሙንን እንቅፋቶችም ሆነ ማታለያዎች ለማለፍ አቅም እንደሚሆን ይገልፃል።

ከሲዳማ ክልል ግንባር ቀደም ኢንተርፕራይዝ በመሆን የአንደኛ ደረጃን በመያዝ የዋንጫና ሰርተፊኬት ተሸላሚ እንደሆኑ የሚናገረው ወጣት ሳሙኤል፤ በሀገር አቀፍ ደረጃም እውቅና በማግኘት ለሌሎች አርአያ መሆን እንደቻሉ ይህም ከምንም ነገር በመነሳት ውጤታማ መሆን እንደቻለ ወጣት ትልቅ ደስታ የሚሰጥ እንደሆነ ይገልፃል።

ከምንም ነገር በመነሳት በአሁኑ ወቅት ወደ አንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ብር ካፒታል ማስመዝገብ የቻሉት ሁለቱ ወጣቶች ባስተላለፉት መልዕክት፤ አዲስ ሥራ ስንጀምር፣ እየሠራንም ከሆነ ሥራችንን ለማስፋት ስናስብ ነገሮች ሁሉ አልጋ በአልጋ ይሆኑልናል ብሎ መጠበቅ ትክክል አይሆንም፡፡ ያለን ገንዘብ፣ የሰው ኃይል፣ የሥራ ቦታ፣ የገበያ ትስስር ወዘተ በምንፈልገው ልክ የመሆን ዕድሉ አነስተኛ ነው። ስለዚህ ያሉንን ነገሮች ቅደም ተከተል በማስያዝና በሁነኛ መንገድ በማቀናጀት መሥራት መቻል አለብን። እንዲህ ማድረግ እንድንችል ደግሞ ነገሮችን የማቀናጀትና ውጤት የማምጣት ክህሎትን ማዳበር ያስፈልገናል ከመሥራት ውጭ አማራጭ የለንም ሁላችንም በሥራ እራሳችንን መለወጥ አለብን ሲል ለወጣቶች መልዕክት አስተላልፏል።

# የምድር በረከት

## ክልሉን ከማዕድን ሀብቱ የበለጠ ተጠቃሚ ስማድረግ

ወርቅነሽ ደምሰው

የኦሮሚያ ክልል በተፈጥሮ ሀብት የታደለ ነው። ከእነዚህ የተፈጥሮ ሀብቶች መካከልም ማዕድናት ይጠቀሳሉ፡፡ በክልሉ የወርቅ፣ የከበሩ ማዕድናት፣ የድንጋይ ከሰል፣ የኢንዱስትሪ፣ የኮንስትራክሽንና ሌሎች ማዕድናት በስፋት ይገኛሉ፡፡ እነዚህን የማዕድን ሀብቶች በማልማት በኩልም አነስተኛና ከፍተኛ አምራቾች እንዲሁም ኩባንያዎች ተሰማርተው ለራሳቸውም ለሀገራቸውም ገቢ እያስገኙ ናቸው፡፡

የክልሉ ማዕድን ልማት ባለሥልጣን መረጃዎች እንደሚያመላክቱት፤ በክልሉ በማዕድን ልማት 804 አነስተኛ አምራቾች እና ከፍተኛ አምራቾች ተሰማርተዋል፡፡ በዘርፉ በተያዘው በጀት ዓመት ግማሽ ዓመት ብቻ በማዕድን ዘርፉ ከአንድ ሺ 314 በላይ ዜጎች ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ እድል አግኝተዋል፡፡

የኦሮሚያ ማዕድን ልማት ባለሥልጣን ዋና ኃላፊ አቶ በዙ ዋቅቤካ በክልሉ እምቅ የማዕድናት ሀብት መኖሩን ጠቅሰው፣ የወርቅ፣ የከበሩ ማዕድናት፣ የድንጋይ ከሰል፣ የኢንዱስትሪ እና የኮንስትራክሽን ማዕድናትን ጨምሮ ሌሎች በርካታ ማዕድናት እንደሚገኙ ያመላክታሉ፡፡

እሳቸው እንደሚሉት፤ ክልሉ ካሉት በርካታ ማዕድናት መካከል ከ60 በላይ ማዕድናት በጥናት ተለይተዋል፡፡ ከእነዚህም መካከል እስካሁን 40 የሚደርሱትን ለማልማት ጥረቶች እየተደረጉ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ እስካሁን ድረስ እነዚህን ማዕድናት በሙሉ ለማምረት የሚያስችል ፈቃድ ወስደው የተሰማሩ ባለሀብቶች የሉም፤ ይህም በአካባቢው ያለውን ዕምቅ የማዕድን ሀብት አልምቶ ሀገርን ተጠቃሚ ከማድረግ አንጻር እምብዛም ያልተሰራበት መሆኑን ያመለክታል፡፡

በማዕድን ልማቱ በኩል አሁን ላይ መሻሻልና ለውጦች እየታዩ መሆናቸውን ጠቅሰው፣ በልማቱ ብዙ ርቀት ለመጓዝ ብዙ መሥራት ይጠይቃል ሲሉ ያመላክታሉ፡፡ በተያዘው በጀት ዓመትም ክልሉ የተለያዩ ማዕድናትን ለማምረት አቅዶ እየሠራ መሆኑን ጠቅሰው፤ ማዕድናት በማልማት ከውጭ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ወደ ሀገሪቱ የሚገቡትን ምርቶች በሀገር ውስጥ በመተካት እንዲሁም ወደ ውጭ በመላክ ማዕድናቱ የውጭ ምንዛሪ እንዲያስገኙ እየተሠራ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

በማዕድን ዘርፉ ለማሳካት ከታቀዱት አራት ግቦች መካከል፤ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ፣ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ መተካት እና የውጭ ምንዛሪን ግኝትን ማሳደግ በሚሉት ላይ ያተኮሩ ሥራዎች እየተሰሩ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

እሳቸው እንዳስታወቁት፤ በማዕድን ዘርፉ በርካታ ቁጥር ያላቸው አምራቾች የተሰማሩ ሲሆን ውጤታማ የሆኑት ግን ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ በክልል ደረጃ ፈቃድ የወሰዱት አነስተኛ አምራቾች 781 ሲሆኑ፤ በፌዴራል ደረጃ ፈቃድ ወሰደው በክልሉ ማዕድን ልማት ላይ የተሰማሩ ደግሞ 23 ከፍተኛ አምራቾች ናቸው፡፡ ከእነዚህ መካከል በአነስተኛም ሆነ በከፍተኛ ፍቃድ ካገኙ አልሚዎች ውስጥ ውጤታማ የሆኑት ጥቂቶች ሲሆኑ፣ አብዛኞቹ ብዙ ሥራ መሥራት ይጠበቅባቸዋል፡፡

አቶ በዙ እንዳሉት፤ በክልሉ ሜድሮክ ኩባንያ ወርቅ በማምረት ውጤታማ ነው፡፡ ሜድሮክም ቢሆን ግን ክልሉ ካለው ሀብትና አቅም አንጻር ከዚህ በላይ መሥራት እንዳለበት ይጠበቃል። በዘርፉ ምን ያህል አምራቾች ተሰማሩ ማለት ሳይሆን ምን ያህሉ ናቸው ውጤታማ የሆኑት የሚለው በደንብ ተፈትሾ መሥራት ይኖርበታል፡፡

በክልሉ በ2016 በጀት ዓመት በማዕድን ዘርፍ በርካታ ሥራዎች መሥራታቸውን የገለጹት ዋና ኃላፊው፤ በማዕድን ዘርፉ ከአንድ ሺ 314 በላይ ለሚሆኑ ዜጎች ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ እድል መፈጠሩንም ተናግረዋል፡፡ በጀት ዓመቱ



**ማዕድን በማምረት ሥራ ላይ በባሕላዊ መንገድ ብቻ ሁለት ሺ463 ፈቃድ አውጥተው እየሠሩ ናቸው፡፡ እነዚህ አካላት ሕጋዊውን መስመር ተከትለው እንዲሰሩ ለማስቻል በተደረገው የማጣራት ሥራ ፈቃድ ወስደው ሕጋዊ በሆነ መንገድ እየሠሩ ያሉት 781 ብቻ ናቸው**

የመጀመሪያ ስድስት ወራት የዘርፉን ችግሮች ለመፍታት መሠራቱን ጠቅሰው፤ በቀጣይ ወራት ደግሞ የተጀመሩ ሥራዎችን አጠናክሮ በማስቀጠል ትልቅ ለውጥ እንደሚመጣ ይታመናል ብለዋል፡፡

በክልሉ ለማዕድን ዘርፉ የልማት ጋሬጣ ከሆኑ ችግሮች መካከል የኮንትሮባንድ ንግድና ሕገ ወጥ የማዕድን ዝውውር፤ አለመረጋጋትና የሰላም እጦት እንዲሁም ቴክኖሎጂ ተጠቅሞ ማምረት አለመቻል ዋና ዋናዎቹ ናቸው ያሉት ዋና ኃላፊው፣ በዘርፉ ያጋጠሙትን እነዚህን ሦስት ጋሬጣዎች ለመፍታት ብዙ መሠራቱንም ገልጸዋል፡፡ ለአብነት ኮንትሮባንድ /ሕገ ወጥነት/ ለመከላከል ኅብረተሰቡን ያሳተፉ የተለያዩ አሠራሮች በመዘርጋት እየተሠራ መሆኑን አመላክተዋል፡፡

እሳቸው እንዳስታወቁት፤ ሕገ ወጥነትን ከመከላከል አንጻር ሕገ ወጥ አካላትን በመለየትም ርምጃ ተወስዷል፡፡ ማዕድን በማምረት ሥራ ላይ በባሕላዊ መንገድ ብቻ ሁለት ሺ463 ፈቃድ አውጥተው እየሠሩ ናቸው፡፡ እነዚህ አካላት ሕጋዊውን መስመር ተከትለው እንዲሰሩ ለማስቻል በተደረገው የማጣራት ሥራ ፈቃድ ወስደው ሕጋዊ በሆነ መንገድ እየሠሩ ያሉት 781 ብቻ ናቸው፡፡ በመሆኑም ከአንድ ሺ 600 በላይ አምራቾች ሕገ ወጥ በሆነ መልኩ ማዕድን እያመረቱ በመገኘታቸው ርምጃ እንደተወሰደባቸው አስታ ውቀዋል፡፡

በተጨማሪም ሕገ ወጥነትና ኮንትሮባንድ ሊከላከል የሚችል ከተለያዩ አካላት የተወጣጣ የማዕድን ኮሚቴ በቦርድ ደረጃ ተቋቁሟል። ኮሚቴው ከክልል ጀምሮ እየሠራ ይገኛል። በዚህም ለውጦች እየመጡ ናቸው፡፡ በዚህ ሥራ ኅብረተሰቡንም በደንብ ማሳተፍ ይገባል። እነዚህን ማነቆዎች ለመፍታት በተደራጀ መልኩ በመሥራት ኮንትሮባንድና ሕገ ወጥነትን መከላከል ለውጦች ማምጣት ይቻላል ብለው እንደሚያምኑም ዋና ኃላፊው ተናግረዋል፡፡

ማዕድን ማምረት ሥራ ላይ የተሰማሩ አምራቾች ቴክኖሎጂ እንዲያገኙና አቅማቸው እንዲዳብር መሥራት ያስፈልጋል ያሉት ዋና ኃላፊው፤ ይህም በአሠራር፣ በመመሪያ፣ በደንብና በአዋጆች እንዲደገፍ ብዙ መሥራትን እንደሚጠይቅ ገልጸዋል፡፡ በሰላም ጉዳይ ላይም የሚመለከታቸው የፀጥታ ኃይሎች ትኩረት ሰጥተው እየሰሩ መሆናቸውን አመላክተዋል፡፡

እንደዋና ኃላፊው ማብራሪያ፤ መንግሥት በተለይ ለማዕድን ዘርፉ በሰጠው ትኩረት ሀገሪቱ የውጭ ምንዛሪ እንድታገኝና ከውጭ የሚመጡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ መተካት እንዲቻል የሚረዱ ሥራዎች እየተሠሩ ናቸው፡፡ የፀጥታ ችግር ባለባቸው አካባቢዎች ያሉት ማዕድናትን ለማምረት ሰላም በማስጠበቅ ረገድ የፀጥታ አካላት የሚሰሩት ሥራ እንዳለ ሆኖ ኅብረተሰቡን ሰላም በማስጠበቅ ረገድ የድርሻውን መወጣት አለበት። በሰላም ረገድም ቢሆን መሻሻሎች ታይተው ለውጦች እንደሚመጡ ይታመናል ብለዋል፡፡

‹‹ክልሉ በማዕድን ሀብት የበለጸገ ቢሆንም፣ ከዚህ ሀብት የሚፈለገውን ያህል ተጠቃሚ አይደለም›› ያሉት ዋና ኃላፊው፤ ለዚህ ምክንያቱ ቀደም ሲል የማዕድን ዘርፍ እምብዛም ትኩረት ተሰጥቶት ባለመሥራቱ ነው ይላሉ፡፡ ዘርፉ በመንግሥት ትኩረት ከተሰጣቸው ዘርፎች መካከል አንዱ ተደርጎ መሠራት ከተጀመረ ቅርብ ጊዜ መሆኑን ጠቅሰው፤ ዘርፉን በቴክኖሎጂ መደገፍ የመጀመሪያው ትኩረት ተሰጥቶት ሊሠራበት የሚገባው ጉዳይ እንደሆነ ያመላክታሉ። ዘርፉን ለማጠናከር አመለካከትን ጭምር መቀየር እንደሚያስፈልግም አስገንዝበዋል፡፡ በዘርፉ የተሰማሩ አምራቾች እውቀትና ብቃት እንዲኖራቸው በቴክኖሎጂ የዳበረ ልምድ እንዲያገኙ መሠራት አለበት ሲሉም ገልጸዋል፡፡

‹‹ማዕድንን ማልማት በባሕሪው ከፍተኛ ካፒታል ይጠይቃል›› ያሉት ዋና ኃላፊው፤ አሁን እየተሠራ ባለበት መንገድ በማዕድን (በባሕላዊ እና በተበታተነ መልኩ) የማምረት ሥራ ላይ ውጤት ማምጣት እንደማይቻልም ያመናሉ፡፡ እነዚህን አምራቾች ወደ አንድ በማምጣትና በማቀናጀት በቴክኖሎጂ እንዲታገዙ ማድረግ ከተቻለ ለውጦች ማምጣት እንደሚቻል ጠቅሰው፤ አሁን መንግሥት በሰጠው ትኩረት ልክ ልማቱ የሚቀጥል ከሆነ ውጤቶች ማምጣት ይቻላል ብለዋል፡፡

አቶ በዙ እንዳስታወቁት፤ የማዕድን ዘርፉን ሥራ ከፖሊሲ፣ ከአዋጆች እና ከሕግ ጋር አቀናጅቶ መሥራት በፋይናንስና በሎጂስቲክ መደገፍ መቻልን እስከ ታችኛው እርከን ድረስ በደንብ መሬት ይዞ መሥራትን ይጠይቃል፡፡ ‹‹ማዕድን ስለተፈለገ ብቻ አይገኝም፤ በማዕድን ላይ ድርሻ ያላቸው አካላት ሁሉ ኃላፊነታቸውን መወጣት ሲችሉ ነው ውጤት ማምጣት የሚቻለው፡፡ መንግሥት ለዘርፉ በሰጠው ትኩረት ብዙ ለውጦች እየታዩ ናቸው፤ ልማቱ እነዚህን አጠናክሮ ማስቀጠልን ይጠይቃል፡፡ በማዕድኑ ዘርፍ የተሰማሩ አካላት በእውቀት ላይ የተመሠረተ ሥራ እንዲሰሩ ያስፈልጋል፡፡ ይህን ሀብት አውቆና ተረድቶ በእውቀት መመራት ይገባል፡፡

በባለሥልጣኑ በኩል የዘርፉን ችግሮች በመፍታት የማዕድን ልማቱን ለማፋጠን እየተሠራ መሆኑን ገልጸው፤ አሁን በማዕድን ዘርፉ የተመዘገቡትን ውጤቶች በማስቀጠል በቀጣይ የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ ብዙ ጥረቶችን ማድረግ እንደሚያስፈልግም ዋና ኃላፊው አስገንዝበዋል፡፡

የክልሉ የማዕድን ልማት ባለሥልጣን ምክትል ኃላፊ ወይዘሮ ትዕግስት ተረፈ በበኩላቸው እንዳሉት፤ በክልሉ በተያዘው በጀት ዓመት ሰባት ወራት ውስጥ በርካታ ማዕድናት ወደ ውጭ ተልከዋል፡፡ በክልሉ በሰባት ወራት ውስጥ የማዕድን ዘርፍ ምርቶችን ወደ ውጭ በመላክ 306 ሚሊዮን 810 ሺህ 980 ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ፤ 163 ሚሊዮን 741 ሺህ 599 ዶላር የውጭ ምንዛሪ ማግኘት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ከማዕድን ዘርፉ ከሀገር ውስጥ ገቢ አንድ ቢሊዮን 368 ሚሊዮን 338 ሺህ 721 ብር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ፤ አንድ ቢሊዮን 36 ሚሊዮን 545 ሺህ 436 ብር ገቢ ማግኘት ተችሏል፡፡

በክልሉ የግንባታና የኢንዱስትሪ ማዕድናት በስፋት ገቢ የሚያስገኙ ምርቶች ናቸው ያሉት ምክትል ኃላፊዋ፤ የወርቅና የጌጣጌጥ ማዕድናት የውጭ ምንዛሪ ከማስገኘታቸው በተጨማሪም ከፍተኛ የሆነ የ“ሮያሊቲ” ገቢ እንዲገኝ ማድረ ጋቸውን ጠቅሰዋል፡፡

እንደ ባዛሌት፣ አሸዋ፣ ኢግኒምብራይት የግንባታ ማዕድናትን ጨምሮ በክልሉ የተለያዩ ማዕድናት እንደሚመረቱ ጠቅሰዋል። እንደ ላይምስቶን፣ ጂፕሰም፣ የድንጋይ ከሰልና የመሳሰሉት የኢንዱስትሪ ማዕድናትን እንደሚ መረቱ ጠቅሰው፣ ከዚህም ስድስት ሚሊዮን 112 ሺህ 268 ቶን ማምረት መቻሉን አስታወቀዋል፡፡

በክልሉ በሰባት ወራት የማህበራትንና የኩባንያዎችን ምርት ጨምሮ አንድ ሺህ 817 ነጥብ 76 ኪሎ ግራም ወርቅ መመረቱን ጠቁመው፣ 16 ሺህ 730 ኪሎ ግራም የጌጣጌጥ ማዕድናት ማምረት ተችሏል ብለዋል፡፡

ለዘርፉ ዋና ተግዳሮት ተብለው ከሚጠቀሱ ጉዳዮች መካከል ሕገ-ወጥ የማዕድናት ምርት ግብይትና አቅርቦት ዋነኛው መሆኑን ምክትል ኃላፊዋ ያመላክታሉ፡፡ በሰባት ወራቱም ከድንጋይ ከሰል ምርት ጋር ተያይዞ ያለው የገበያ ችግር ፈታኝ መሆኑን ጠቅሰው፤ እነዚህን ችግሮች ለመፍታትም በክልሉ ያሉትን የማዕድን ምርት ፈቃዶች በሙሉ በአዲስ መልክ ለማድረግ ከወረዳ ጀምሮ እስከ ክልል ድረስ ከፍተኛ እንቅስቃሴ መደረጉን ጠቁመዋል፡፡ በዚህም አምራቾቹ ሕጋዊ መስመርን ብቻ ተከትለው እንዲሰሩ ከፍተኛ ሥራ መሥራቱን አመላክተዋል፡፡ ሕጋዊ አሠራር የማይከተሉ አምራቾችንም በመለየት ሕጋዊ ርምጃ እንዲወሰድባቸው መደረጉንም ጠቅሰው፣ በዚህም መሠረት የግንባታና የኢንዱስትሪ ማዕድናት ምርት ከፍተኛ መሻሻል አሳይቷል ሲሉ አስታውቀዋል፡፡

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## ሕይወት፣ ናፍቆት፣ ትዝታና ፍቅር

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ናፍቆት እንዳረበበበት፣ ትዝታ እንደሰፈረበት፣ በፍቅር ገሰስ አጋሰስ እንደቆመ ሕይወት ምን ውበት ምን ጥያሜ አለ? ሄደን ሄደን አለመቆም ቢኖር.፣ ናፍቀን ናፍቀን አለመርሳት ቢኖር ያን ነበር ሕይወት የምለው:: መጨረሻው በተሰወረ መጀመሪያ ላይ ሰውና ባለታሪክ መሆን...ነገን ባለማወቅ ውስጥ በተስፋ መዳከረ ይሄም የምፈራው ነው:: እንደሰው ከተሰጡኝ የምሰጋው::

ተፈጥሮ ከብዙ ስሜቶች ውስጥ የቀለመን የእንባና ሳቅ ስዕሎች ነን:: ሰው የእንባና ሳቅ ስዕል:: ይሄን ለመረዳት ወደትናንት አሻቅቡ ወደዛሬ አጎንብሱ..አልረሳ ያሏችሁን የሳቅና እንባ ድልብ ታሪኮች እንደምትጋፈጡ በወላዲቷ እምላለሁ:: መቼ ደልቶን ብቻ ያውቅና? መቼስ እንደፈነጠዝን ቀረንና? አንድንም ካልናቸው ትካዜዎች ታክመን የለ..? ባላለፉ ካልናቸው ጊዜና አጋጣሚዎች ተላልፈን የለ? ካደሙን የሆኑ ነገሮቻችን አገግመን የለ? የማያልፉ ከሚመስሉን፣ እንዲደገሙ ከምንፈልጋቸው የሳቅ አለሞች ወጥተን የለ? ተመልሰው እንዳይመጡና ተመልሰው እንዲመጡ በማንከጅላቸውና በምንከጅላቸው ትናንትናዎቻችን ስር በአፍ ጢማችን የተደፋን ነን:: ይነስም ይብዛም በፍቅር በኩል፣ ሰው በመሆን ግድም የተዋሃዱንን የሕይወትን ወያባና አይነግቡ የናፍቆትና የትዝታ በትር ቀምሰናል...ሰንበሩም አሁን ድረስ አለ:: እኔም ይሄን ስጽፍ እናተም ይሄን ስታነቡ እንኳን ባልተመሳሰለ ስሜት ውስጥ ሆነን ነው::

መጨረሻው በተሸሸገ መጀመሪያ ላይ ለመኖር ተስፋን መቋጠር በሰው ልጅ ላይ የፈጣሪ ታላቁ ሴራ እለዋለሁ:: ካልሆነ ትናንት በዛሬ ሲጠራ ነገን ከዛሬ መሰወሩ ለምን ሆነና? መቼም እኛ ሰዎች አልሆን ሲለንና እንዳሳባችን ሳይሆን ሲቀር ነቃፊና አቃቂር አውጪዎች ነን:: ከዘፍጥረት ጀምሮ ዛሬም ድረስ ሰው የፈጣሪ ባላንጣ ነው:: አዳምና ሄዋን አምላክነትን ሻቱ፣ ሊቀመላዕክት ሳጥናኤል ፈጣሪ ነኝ አለ...ናቡከደነጾር ጌታ እኔ ብቻ ነኝ አለ..እናስ ጠላቱ አይደለንም?

እግዜር ለሁልጊዜም ከሰው ያፈነገጠ ነው...እንዳሳባችን አያስብም:: ፈጠረን ገነት አኖረን..ገነት ውስጥ ካሉ ዛፎች ሞት ካለባት ከዚች እጸ በለስ በቀር ሁሉን ብሉ ሲል ነጻነትን ሰጠን:: በነጻነታችን መሀል ራስ ወዳድነትን ዶለን አትብሉ የተባልነውን በላን..ከገነት ተባረርን፣ ተረገምን፣ የሞት ሞትን ሞትን:: ይሄ ሁሉ ያለመታዘዛችን ዳፋ እንደሆነ ሳይገባን በእግዜር ላይ ጣትን መቀሰር ምን የሚሉት ውንብድና ነው? ከበላን በኋላም በበደላችን ሳይቆሸሽ ከክብሩ ዝቅ ብሎ በሞት ታረቀን::

አንዳንድ ጊዜ ወደአእምሮዬ የምትመጣ ለማመን አስቸጋሪ የሆነች ሀሳብ ብጤ አለችኝ..እግዜር ነገን ከሕይወት መደበቁ፣ መጪውን ከዛሬ መሸሸጉ ከሰጠን የተስፋ ሕይወት ዳግመኛ እንዳንሸራተት ሊታደገን ቢሆንስ የምትል:: ይቺ ሀሳብ ከብዙ መጠየቅ በኋላ ያገኘኋት እኔን ብቻ የምትወክል የግል መልሴ ናት::

እንደነገ የሰው ልጅ ምን ባዳ፣ ምን በርሀ..ምን ጨለማ አለው? ነገ እኮ የአለመኖር አንድ ሁለተኛው ነው..:: አለመኖርን ናፍቆ መጠበቅ ማንም ያላበደው እብደት ነው:: የተሰጠንን አሁን ሳንኖር በራቀን ነገ መጨነቃችን አማኑኤል የሚያስገባ ሌላው እብደታችን ነው:: ግን ከመጠበቅና ተስፋ ከማድረግ ውጪ አማራጭ የለንም..

በናፍቆት የተለበጡ አንዳንድ ቀኖችን እንደማስታወስ፣ እንደማውሳት ያለ ህመም የለም:: ማስታወስ የማን ፈልጋቸውን አንዳንድ ነገሮች የሚዘነጋ የሰውነት ክፍል ቢኖረን የሚለው ከምኞቶቼ መሀሉን ነው:: ዋና ህመም ሆኖ የሚመጣው ደግሞ ላለማስታወስ ማስታወስ ነው:: ለመርሳት በሞከርናቸው ቁጥር በሚታወሱን..ላለመርሳት በጣርን ቁጥር በሚረሱን ነገሮች መሀል ሰው መሆን ከባዱ ፈተና ነው:: መቼም ላለማስታወስ መሞከር መቼም ላለመርሳት እድል መስጠት ነው:: ኤጭ..

አንዳንድ ቀንን ማውራት ያህል ህመም የለም:: አንዳንድ ሰውን መራቅ ያህል ዋይ ዋይ የለም:: ሕይወት ‹በበርቺና በሁሉም ያልፋል› እንዳትሸር ሆና የጎበጠችበት ማንም የማይደርስበት ቦታ አለ:: ሊያቃኑት ሲሉ የሚሰበር፣ ሊያሸሩት ሲሉ የሚመረቅዝ፣ ሊረሱት ሲሉ የሚያገረሽ::

ናፍቆት ግን ከምንድነው የተሰራው? ትዝታና ፍቅር ያሉበት ሕይወት ምን ይሆን ንጻሬው? ሁሉም ሰው ትናንትን ተሸክሞ የሚኖር ነው:: በእድሜያችን አመሻሽ በብዙ እንባና ባለመሳቅ ስዕል የምናወጋው እልፍ የታሪክ ባለቤቶች ነን:: እስኪ ልባችሁን በርብሩት ከሆነ ሰው ጋር የሆነ ቦታ በሆነ አጋጣሚ እንዠርግ ታሪክ አላችሁ:: ስትታወስ በምትገርም አጋጣሚ...ይሆናል ተብሎ ባልተገመተ ሁኔታ ለትካዜ የጣሉን ብዙ ናቸው:: የማንረሳው ሰው፣ የማንረሳው ቀን፣ የማንረሳው ወርና ዓመት የትዝታችንን ገሳ ለብሰው ወደዛሬ በማጨንቆር አሉ:: አይመጡም እንሄድባቸዋለን እንጂ..:: ለሌላ ታሪክ ስሎች ሆነን በዛሬ አከርካሪ ላይ ቆመናል..ትናንት ሲሆን በትዝታ ለምንወድቅበት ታሪክ:: ትናንት እንደውብ ከተማ በልባችን ላይ አሽብርቆ አለ:: በሆነ ሰው..የሆነ ቦታ.. በሆነ አጋጣሚ ያረበበ:: ለእያንዳንዳችን የማይፈርስ ከተማ ነው..የዛሬ ውበት የማያደበዝዘው..የነገ ተስፋ የማያወግገው.. ባለቀለም ከተማ::

ናፍቆት የነፍስ ሰንበሯ ነው እላለው..በሆነ ሰው የሆነ ጊዜ ላይ የተገረፈችው..የተሳመችው:: ከንፈርም አለንጋም የናፍቆት ሰንበር አላቸው..ነፍስ ላይ የሚያርፍ:: በነፍስ ገላ ላይ የንጹህ ከንፈርን ማህተም ያህል ናፍቆት ታውቃላችሁ? በአማኝ ልብ ላይ የከሀዲ ሰውን ያህል ጥዝጣዜ አለ? ሁለቱም በየፊናቸው ያማሉ..:: ገፍቶን ለሄደም ሆኖ አጽንቶን ለሄደ ጥንድ እንባ አለን..ባረፈብን ጥላቸው ስር የሆነውን እያሰብን የምንሆነው::

ናፍቆትን እንደቤት ጥራጊ ከህይወት አውላላ ላይ ጠራርጎ የሚያጠፋ መድሀኒት ወይም ግኝት ቢኖር አልረሳኝ ያሉ አንዳንድ ሰዎችን..አንዳንድ ቀኖችን..አንዳንድ አጋጣሚዎችን ለመርሳት እኔ ነበርኩ ማልጄ የምሸምተው::

ናፍቆት ስለት ነው ነፍስን ገዝግዞ የሚያደማ..ደሙ ዘላለማዊ ነው:: ሞት ካልሆነ ሕይወት የማይከልለው:: ትዝታ በመኖር የተሳለ ስል ፈላጻ ነው..የነፍስን ነገ ገርስሶ የሚጥል:: ትናንት የዛሬና የነገ..ዛሬ የመጪውና የለጣቂው ሾተል እንደሆነ ያልገባው..አሁን የከርሞ ደም እንባ እንደሆነ ያልተረዳ በትካዜ ካራ ራሱን ሊሰዋ ዳዴ ላይ ነው::

ከሁሉም የሚበልጡ አንዳንድ ገጾች አሉ..ከምንም የማይስተካከሉ ጥላማ ተሲያት:: ቆንጆ ሴት ስተት ያለችበት ልብ ጽላት እንዳለበት መቅደስ ነው:: የቆንጆ ሴት ዳና በታሪክ ላይ አሻራው እንዳይጠፋ እንደሚፈለግ ጀብድ ነው:: አይሆኑ መሆኛ:: ከሁሉም ናፍቆት ቆንጆ ልጅ ገብታ የወጣችበት የልብ ህመም ይበልጣል:: እረ እንደሱ አይደለም..ናፍቆት ትንሽና ትልቅ፣ አባጣና ጎርባጣ የለውም። ትላንት ሲሆን ሁሉም ዛሬ ተሲያት ነው..

እንዴት ገብታ እንደወጣች ሳስበው ለሁልጊዜ ይገርመኛል:: አገባቧ መቼም ላለመውጣት ስለሚመስል መቼም አጣዋለው ያላልኩትን ታሪኬን አውርሻት ነበር:: ለካ ሰው በምሥራቅ ታይታ በምዕራብ እንደምታሽቆለቁል ጀምበር ነው:: በፍቅር ማበል ምን የሚሉት ስልጣኔ ነው? አስታውሳለው ከእሷ ጋር የተቀጣጠርንባትን የቅዳሜ ከሰዓት ስጠብቅ..አስታውሳለው ከፊቴ ያሉት ሀሙስና አርብ የዘላለም ያህል ርቀውኝ ሲያስተክዙኝ.. አስተውሳለው መንፈቅ ለሰነበተ ፍቅራችን የሚሆን ስጦታና ፍቅር አዘጋጅቼ ወደእሷ እንደሄድኩ..ትዝ ይለኛል አጠገቧ ስቆም በህይወቷ ያልመጣ ደስታን ልፈጥርላት ተሰናድጄ እንደነበር..አስታውሳለው ስለብሰው እንደምትወደው በምትነግረኝ አለባበስ ፊቷ እንደቆምኩ፣ ፍቅሬን በቃልና በአበባ ልገልጽላት በአፌ በጎ ቃላትን በእጄ ደግሞ ፍቅር ነጋሪ ቀይ አበባ እንደታቀፍኩ...አስታውሳለው ወደእሷ ስሄድ በምን ኩራት ውስጥ እንደነበርኩ..አስታውሳለው በሕይወቴ አዲስ ታሪክ ልጽፍ እንደተዘጋጀሁ..አስታውሳለሁ ሳገኛት ግንባሯን ስሜ እንደምትወደው ወደማውቀው ወደሆነ ቦታ ወስጄ ላስደስታት ከራሴ ጋር እንደተማከርኩ..አስታውሳለው ከእሷ ጋር ብዙ ህልሞቼን..አስታውሳለው ተጋብተን ብዙ የደስታ ዓመታትን እንደምናሳልፍ ሳስብ.....እና ምን ሆነ አትሉኝም? የታሪኬ ደማቋ ሴት በአንድ ቀጭንና ነሆለል ቴክስት ‹አልመጣም አጠብቀኝ..ብላ ላለመመለስ ከህይወቴ መውጣቷን የነገረችኝ..

ጥሩም ይሁኑ መጥፎ በታሪኬ ላይ የተሰመሩ አንዳንድ መስመሮች የሕይወት ስዕሎቼ ናቸው:: ያለፍኩበትን እንደካሴት ቀድተው ያስቀመጡ..በናፍቆት አለንጋ የሚቀጡኝ::

# ዓለም አቀፍ

## የአየርላንዱ ጠቅላይ ሚኒስትር ሥልጣን ሊለቁ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



የፓርቲያቸው ፋይን ጋኤል ሊቀመንበር መሆን የቻሉት ሊዮ ቫራድካር፣ የአየርላንድ በዕድሜ ትንሹ ጠቅላይ

የአየርላንዱ ጠቅላይ ሚኒስትር ሊዮ ቫራድካር በገዛ ፈቃዳቸው ሥልጣን ሊለቁ መሆኑን አስታወቁ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሥልጣን መልቀቃቸውን ባስታወቁበት ወቅትም "ሀገራቸውን የመሩበት ዓመታት በሕይወታቸው የተሳካ ተግባር ያከናወኑበት" እንደሆነም ገልጸዋል። ከፓርቲ ሊቀ መንበርነታቸው ወዲያውኑ የሚነሱ ሲሆን፤ ተተኪ ጠቅላይ ሚኒስትር ከተመረጠ በኋላ ደግሞ ሥልጣናቸውን ይለቃሉ ተብሏል።

ከሥልጣን የለቀቁትም በ"ግላዊ እና ፖለቲካዊ" ምክንያቶች እንደሆነም ተናግረው "ለዚህ ኃላፊነት የተሻለው ሰው አይደለሁም" በማለት ተናግረዋል።

በአውሮፓውያኑ 2017፣ በ38 ዓመታቸው ሚኒስትር በመሆን ታሪክ ሠርተዋል።

በአሁኑ ወቅት በደብሊን መቀመጫውን ያደረገውን የጥምር ፓርቲዎች መንግሥት ከፊያና ፌይል እና ግሪን ፓርቲ ከተሰኙት ፓርቲዎች ጋር እየመሩ ይገኛሉ።

ንግግር ያደረጉት ጠቅላይ ሚኒስትር አየርላንድን ከሥራ አጥነት እንደታደጓት እንዲሁም ከበጀት ጉድለት ወደ በጀት ትርፍ እንዲሁም ከምጣኔ ሀብት መሽመድመድ አውጥተው ወደ ብልጽግና እንደመሯትም ተናግረዋል።

በተለይም በአየርላንድ "የሕፃናት መብትን በማስከበር፣ ለተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪዎች ማኅበረሰብ እና ለሴቶች እኩልነት በመሥራት ሀገራቸውን ዘመናዊ እና እኩልነት የሰፈነባት በማድረጋቸው ኩራት ይሰማኛል ብለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሥልጣን ዘመናቸው የተመሳሳይ ጾታ ጋብቻ እና ጽንስ ማቋረጥን ሕጋዊ እንዲሆን ለማድረግም የአየርላንድ ሕገመንግሥትን ለመቀየር የተደረጉ ሕዝበ ውሳኔዎችን ደግፈዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሥልጣናቸው ዘመን ሌሎች አሳካኋቸው ብለው የጠቀሷቸው የሕፃናት እንክብካቤ ተደራሽነትን ማሻሻል እንዲሁም መንግሥት በሥነ ጥበብ፣ ባህል፣ ዓለም አቀፍ ልማት እና የሕዝብ መሠረተ ልማቶች ላይ የሚያደርጋቸውን ወጪዎች መጨመር ይገኙበታል።

ሆኖም "ያልተሳካልን አንዳንድ ዘርፎች አሉ" ሲሉም ተናግረው፤ "በእንደዚህ አይነት ቀን ሌሎች ነቅሰው እንዲያወጧቸው ብተወው ይቅር እንደምትሉኝ ተስፋ አደርጋለሁ" ብለዋል።

አሁን ያለው መንግሥት "እንደገና ሊመረጥ ይችላል" ቢሉም፤ ነገር ግን "ከእንግዲህ ለኃላፊነቱ የተሻለው ሰው እንዳልሆንኩ" ይሰማኛል ሲሉ ተናግረዋል።

## የቀድሞ የፖሊስ አባል 40 ዓመት ተፈረደበት

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

በአሜሪካ ሚሲሲፒ ግዛት የፖሊስ አባል የነበረው ግለሰብ ከሌሎች አምስት ባልደረቦቹ ጋር ሆኖ ሁለት ጥቁር አሜሪካውያንን በቤት ውስጥ በማሰቃየቱ የ40 ዓመት እስር ተበይኖበታል።

ክርስቲያን ዴድሞን የተባለው የቀድሞ የፖሊስ መኮንን ከባልደረቦቹ ጋር ባለፈው ዓመት ጥር ወር ላይ ለፈጸመው ወንጀል ነው ቅጣት የተጣለበት።

ሌሎች ሦስት የፖሊሰ መኮንኖች ደግሞ በድምሩ የ54 ዓመታት እስር ተፈርዶባቸዋል።

ማይክል ጄንኪንስ እና ኤዲ ፓርከር የተባሉት ጥቁር አሜሪካውያን በፖሊስ መኮንኖቹ በመሳሪያ ሰደፍ የተደበደቡ ሲሆን ወሲባዊ ጥቃትም ደርሶባቸዋል።

አንደኛው ተጠቂ ጄንክሰን ችሎት ላይ በጠበቃው አማካኝነት ባስነበበው ጽሁፍ 40 ዓመት የተፈረደበት የቀድሞ መኮንን ከፍተኛውን ስቃይ ያደረሰበት እንደሆነ ገልጿል።

“ዴድሞን በአሜሪካ ውስጥ የመጥፎ ፖሊስ መኮንኖች ምሳሌ ነው” ሲለም አክሏል።

የቀድሞው የፖሊስ መኮንን ተበዳዩ ላይ ከመግደል መለስ ያሉ ጥቃቶች ሲያደርስ አፉ አካባቢ ላይ ተኩሶበታል። በዚህም ምክንያት ጄንክስን እስካሁን ለመናገር ይቸገራል።

በአንዲት ነጭ ቤት ውስጥ ጥቁር አሜሪካዊ




በመቆየቱ እና በነበሩ አጠራጣሪ ድርጊቶች የአካባቢው ነዋሪዎች ጉዳዩን ለፖሊስ አሳውቀዋል። ፖሊሶቹ ጥቃቱን እየፈጸሙም በስልክ ይነጋገሩ ነበር።

ለአንድ ሰዓት ከሰላሳ ደቂቃ ያህል ጄንኪንስ እና ፓርከር እጃቸው ታስሮ ሲደበደቡ እና የዘረኝነት ጥቃት ሲደርስባቸው እንደነበር ተመላክቷል።

የአሜሪካ የአውራጃ ፍርድ ቤት ዳኛው ቶም ሊ ዲድሞን ሁለት ጥቁሮች እና ከአንድ ሳምንት ቀደም ብሎ ደግሞ አንድ ነጭ አሜሪካዊ ላይ “እጅግ አስደንጋጭ፣ አሰቃቂ እና ጭካኔ የተሞላበት ድርጊት” ፈጽሟል ብለዋል።

ዴድሞን 40 ዓመት እንደተፈረደበት ከመታወቁ አስቀድሞ ሌላኛው ባልደረባው ኦፕዴክ 17 ዓመት ከ 6 ወር ተበይኖበታል።

ብሬት ማክአልፒን እና ጆሽዋ ሃርትፊልድ የተባሉት የቀድሞ የፖሊስ መኮንኖችም በተመሳሳይ የብይን ውሳኔ ይተላለፍባቸዋል።

# ነፃ ሃሳብ

# የመናኸሪያዎቻችን...

ከ5ኛው ገጽ የዞረ

በሀገራችን "የዓለም የመፀዳጃ ቤት ቀን" በየዓመቱ ሲከበር "በተሻሻሉ የመፀዳጃ ቤቶች በመጠቀም ተላላፊ በሽታዎች በህብረተሰቡ ላይ የሚያደርሱትን የጤና ችግር መከላከል እንደሚቻልና ለዚህም በቅንጅት መሥራት እንደሚገባ የጤና ሚኒስቴር ገለጸ፡፡" ከሚለው ዜና በስተቀር ስለ መፀዳጃ ቤቶች ሲነገር መስማት ብርቅ ነው። "የተሻሻሉ የመፀዳጃ ቤቶችን በመጠቀም እንደ አተት የመሳሰሉ የወረርሽኝ በሽታዎች የሚያደርሱትን የሞትና የሕመም ስቃይ ለመከላከል" ብዙ መሥራት እንደሚገባም እንደዚሁ።

በየዓመቱ በኅዳር ወር በዓለም አቀፍ ደረጃ ለስድስተኛ ጊዜ፤ በሀገር ደረጃ ደግሞ ለሶስተኛ ጊዜ የተከበረውን የዓለም የመፀዳጃ ቤት ቀን በማስመልከት የጤና ሚኒስትር ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች "ህብረተሰቡ የተሻሻለ የመፀዳጃ ቤት መገንባትን አስፈላጊነት፣ አያያዝ እና በአግባቡ መጠቀምን እንዲያጎለብት፤ በተጨማሪም በትምህርት ቤቶች፣ በገበያ ሥፍራዎች፣ በአውቶብስ መናኸሪያዎችና በመሳሰሉት የጋራ መፀዳጃ ቤቶችን መገንባትና ጥቅም ላይ ማዋል ያለውን ጠቀሜታ እንዲረዳ ማድረግ የበዓሉ መከበር ዋና ዓላማ" እንደሆነ የገለፁትን እዚህ ጋ እንደ አንድና በቂ ማስረጃ አድርጎ ማቅረብ ይቻላል።

ኃላፊዎቹ "በሀገር አቀፍ ደረጃ ስምንት የሚሆኑ ሴክተር መሥሪያ ቤቶች በጋራ በመቀናጀት በተለይ በከተሞች ያለውን የመፀዳጃ ቤት ችግር ለማቃለል አዲስ የአሠራር ቅንጅት በመንደፍ ወደ ሥራ" ገብተዋል ብለው የነበረ መሆኑንም አንስቶ መሞገት ያስኬዳል። ጥያቄው "በአውቶብስ መናኸሪያዎችና በመሳሰሉት የጋራ መፀዳጃ ቤቶችን መገንባትና ጥቅም ላይ ማዋል" የሚለው ካላከራከረ በስተቀር ማለታችን ነው።

በፈረንጆቹ 2018 ከጤና ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው ከሆነ ሀገር አቀፍ የመሠረታዊ የመፀዳጃ ቤት ሽፋን 72 በመቶ ደርሷል። "በኢትዮጵያ 93 በመቶ የሚሆነው ሕዝብ መሠረታዊ መፀዳጃ ቤት በቤቱ እንደማያገኝ፤ ከሰሀራ በታች ብቻ 340 ሚሊዮን የሚሆነው ሕዝብ በቂና መሠረታዊ የመፀዳጃ አገልግሎት የሌለው መሆኑን የሚገልጸው፤ የወቅቱ የቢቢሲ ዘገባ ይህንን አይቀበልም) ይህ በእውነቱ ደስ የሚል አፈፃፀም ነው። ግን ደግሞ ምን ያህሎቹ በተገቢው መንገድ ስራ ላይ ውለዋል የሚለው ከታየ አፈፃፀሙን ጥያቄ ውስጥ ይከተዋልና ሊታሰብበት ይገባል።

ለሕዝብ ደህንነትና ጤና፤ ለከተሞች ፅዳትና ተዛማጅ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ሥነ ልቦናዊ ጉዳዮች የሚታሰብ ከሆነ "በተለይ ከመኖሪያ ቤት ውጭ በአብዛኛው የሚፀዳዱት የጎዳና ተዳዳሪዎች መሆናቸው አሌ አይባልም፡፡ ስለሆነም የጎዳና ተዳዳሪዎችም ሆኑ የመፀዳጃ አገልግሎት የማያገኙ ወገኖች በሕዝብ መፀዳጃ ቤቶች ሊጠቀሙ የሚችሉበትን መንገድ ማመቻቸት፤ የምክር አገልግሎትም መስጠት ያስፈልጋል" የሚሉ ጥናታዊ ዘገባዎች ትኩረትን ሊያገኙ የግድ ይሆናል።

በትኩረቱም ቀዳሚ ተተኳሪዎች የመናኸሪያ ዓይነት መፀዳጃ ቤቶች መሆናቸውንም ልብ ማለት ተገቢ ነው። የደንብ ማስከበር ባለሥልጣን ‹‹መንገድ ላይ ሲሸና የተገኘ 200 ብር ቅጣት ይጠብቀዋል›› (ደንብ ቁጥር 150/2015) የሚል መመሪያ ማውጣቱን ተከትሎ "ይሄ መፍትሔ አይሆንም" የሚሉ ሰዎችንም ማዳመጥ ያስፈልጋል። "መንግሥት ተንቀሳቃሽ የሆነ የመፀዳጃ ቤቶችን በየቦታው ማስቀመጥ" አለበት የሚለውም አስተያየት ገራገር ቢመስልም ፍሬ አያጣምና ልብ ሊባል ይገባል።

**ገንዳው ወረፋ ስለነበረና አብዛኞቹ የመፀዳጃ ክፍሎች ነፃ ቢሆኑም፣ በንፅህና እጦረት ተሰቃይተዋል። ሰው ገብቶ ይፀዳዳ ዘንድ አይደለም ዓይኑን እንኳን ወርወር ያደርግ ዘንድ አይጋብዙም**

ቢቢሲ ለንባብ አብቅቶት እንደ ነበረው፣ ጆሴፍ የተባለ የኬንያ ከፍተኛ ፍርድ ቤት (የካቲት 2020) ዜጎች መፀዳጃ ቤት ማግኘት ሕገ-መንግሥታዊ መብታቸው መሆኑን በመጥቀስ የኬንያ መንግሥት ለዜጎቹ መፀዳጃ ቤቶችን እንዲገነባ ወስኗል፣ ለዚህ ውሳኔ ካበቁት ምክንያቶች መካከል፤

ኬንያ ውስጥ ክፍለ ሀገራትን በመኪና ማቋረጥ ከባድ የሚያደርገው የሕዝብ መፀዳጃ ቤቶች ጉዳይ ነው። "የሕዝብ ማመለሻ ውስጥ ሆነው ሽንትዎ ቢመጣስ?" ሲል የሚጠይቀው ይህ ለውሳኔ የሚጋብዝ አስተያየት "ባለሥልጣናት መንገዶችን ሲያስገነቡ ስለ መፀዳጃ ቤቶች ጭራሽ አላሰቡም" ሲል ይወቅሳል። «የሕዝብ ማመለሻ አውቶብስ ሾፌሮች ድንገት ያሻቸው ቦታ ያቆማሉ። ከዚያ ሰው ወዳገኘው ጥሻ ጠጋ ብሎ ተንፈስ ይላል። እንደው ግድ ስለሆነ እንጂ ሴቶችም፣ ወንዶችም ሆኑ ሕፃናት በዚህ መልኩ ሲፀዳዱ ማየት» የተለመደ ነውና ይህ ሊወገድ፣ ችግሩም ሊቃለል ይገባል። የሚሉት በዋናነት ይጠቀሳሉ።

ተቋሙ ለድምዳሜ ያመቸው ዘንድ ያነጋገራቸው ግለሰቦች "መንገድ በመገንባት እጃቸው ያለበት የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች መፀዳጃ ቤቶችን አልገነቡም፤ መፀዳጃ ቤቶችን ማግኘት ደግሞ የዜጎች ሕገ-መንግሥታዊ መብት ነው" ማለታቸውንም በመከራከሪያ ነጥቦቹ ላይ አስፍሯል። ተቋሙ "ሰዎች ያለ ፍላጎታቸው ሜዳ ለሜዳና ጥሻ ውስጥ ለመፀዳዳት መቀመጣቸው ሰብዓዊነታቸውን የሚያወርድ ነው። ሰዎች የተፈጥሮ ግዴታቸውን በጊዜው መወጣት ሲገባቸው መንግሥት ቦታ ባለማዘጋጀቱ ምክንያት እየተሰቃዩ ነው"በማለትም ክሱን ያጠናክራል። ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ካዳመጠ በኋላ ብይን የሰጠ ሲሆን፤ መንግሥት መፀዳጃ ቤቶችን በራሱ ወጪ ለዜጎች እንዲያመቻች አዟል። ይህ ለጠቅላላ እውቀት በመሆኑ እዚሁ ላይ እናቆመዋለን።

ማንም እንደሚያውቀው የመፀዳጃ ቤቶች ጉዳይ የቅንጦት ጉዳይ አይደለም። የመፀዳጃ ቤቶች ጉዳይ የምርጫ ጉዳይም አይደለም። የመፀዳጃ ቤቶች ጉዳይ የግዴታ ጉዳይ ነው። የመፀዳጃ ቤቶች ጉዳይ ከተፀዳጂው ቁጥጥር ውጭ የሆነ ጉዳይ ነው። የመፀዳጃ ቤቶች ጉዳይ መሠረታዊ የጤና ጉዳይ ነው። በአጠቃላይ፣ የመፀዳጃ ቤቶች ጉዳይ የሰዎች መሠረታዊ መብቶችና የዜጎችን ጤና የመጠበቅና አለመጠበቅ ጉዳይ ነው። በመሆኑም፣ ይገነቡ፣ በአግባቡም ይያዙ ዘንድ ሁሉም ነገር ያስገድዳል።

እኛ ሀገር ሆነ እንጂ እንደ አደጉት ሀገራት ቢሆን በመፀዳጃ ቤቶች ጉዳይ ብቻ ስንትና ስንት ሰዎችና ተቋማት ለፍርድ በቀረቡ፤ የሥራቸውን ዋጋም ባገኙ ነበር። እኛ ሀገር ሆነ እንጂ፣ መፀዳጃ ቤቶችን የተመለከቱ፤ ራሳቸውን የቻሉና ተገቢነት ያላቸው ስንትና ስንት አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ወጥተው ሥራ ላይ በዋሉ ነበር። ግና ምን ያደርጋል፤ እኛ ሀገር ሆነና ሁሉም እየሆነ ባለመሆኑ በየመንገድና ጥሻው መፀዳዳት ግድ ሆኗል።

የአሜሪካውን "ARA" (የአሜሪካ መፀዳጃ ቤቶች ማህበር - American Restroom Association) የመሳሰሉ መብትና ሕግ አስከባሪ ብሔራዊ ተቋማት ቢኖሩን ኖሮ በመፀዳጃ ቤቶች በኩል እነዚህ ሁሉ ጉድፎችና ድክመቶች ባልኖሩብንም ነበር።

"መናኸሪያዎቻችን መፀዳጃ ቤቶች አሏቸው ወይ?"ተብሎ ካልተጠየቀ በስተቀር በየመናኸሪያው ያሉ (እንደ ነገሩም ቢሆን) መፀዳጃ ቤቶች ድራማዊ በሆነ መልኩ አስቂኝ ናቸው። ባለቤታቸው ማን እንደሆነ እስከማይታወቁ ድረስ እያደናገሩን ይገኛሉ። ግለሰቦችን በገንዘብ ለመደጎም ይሁን/አይሁን የተቋቋሙት መለየቱ ግር እስኪል ድረስ ያወናብዳሉ።

"ዜጎች ጤንነት የሚባል ነገር አያስፈልጋቸውም" የተባለ እስኪመስል ድረስ የንፅህና ጉድለታቸው ካገር ያስወጣል። ሱስ ልባቸው እስኪጠፋ ድረስ ጭውት ያለባቸው ጥቂቶች እንደ ፈለጋቸው የሚዘውሯቸው የማህበራዊ አገልግሎት መስጫ ሥፍራዎች ናቸው። (በላም በረቱ መናኸሪያ የተመለከትነው ይሄንን እንጂ ሌላ አይደለም።)

በዚህ መናኸሪያ መፀዳጃ ቤቶቹ (የሁለቱም ፆታዎች) በጥሩ ሁኔታ በሕዝብ ሀብት የተገነቡ ናቸው። ሰፋ፣ ለቀቅ ተደርገው የተሠሩ ሲሆን፣ እስከ ውስጥ - መቀመጫዎቹ ድረስ ፈታ ብለው ይቀመጡ ዘንድ ታስቦባቸው ስለ መገንባታቸው እራሳቸው ይናገራሉ። ታዲያ ምን ያደርጋል . . .

መጋቢት 1 ቀን 2016 ዓ.ም ከሰዓት በኋላ ከደብረ ዘይት በመምጣት መውረጃዬን ላም በረቱ መናኸሪያ አደረኩ። የውሃ ሽንት አገልግሎት ማግኘት ፈለግሁና አንዱን ጠየኩት። በእጁ ጣት አመላከተኝ። ሄድኩ። በምስል ጭምር በተደገፈ መልኩ "የወንዶች" እና "የሴቶች" በበር ተለይቶ ተዘጋጅቷል። ቁጭ ብለው ገንዘብ የሚሰበስቡትን ሴትዮ አልፌ ወደ "የወንዶች" ገባሁ። ገንዳው ወረፋ ስለነበረና አብዛኞቹ የመፀዳጃ ክፍሎች ነፃ ቢሆኑም፣ በንፅህና እጦረት ተሰቃይተዋል። ሰው ገብቶ ይፀዳዳ ዘንድ አይደለም ዓይኑን እንኳን ወርወር ያደርግ ዘንድ አይጋብዙም። ግድ ነውና እንደ ምንም ተጠቅሜ ወጣሁ።

ስገባ አልፌ የገባኋቸውን ሴትዮ ስመለስም ማግኘት ግድ ነውና ተገናኘን። ለውሃ ሽንት 5 ብር ይፈልጉ ኖሯልና እጃቸውን ዘረጉ። እኔም ቦርሳዬን ከኋላ ኪሴ እያወጣሁ ሃሳብ መስጠቴን ቀጠልኩ። (እዚህ ላይ "መንግሥታዊ የሆኑት መናኸሪያዎች የሚያስከፍሉ ከሆነ፣ የግል ሆቴሎች ቢያስከፍሉ ምኑ ነው የሚገርመውና ነው አንድ ሰሞን ሲዋከቡ የነበረው?" የሚል ሃሳብ ማንሳት ተገቢ ይሆናል።)

"ሽንት ቤቱ እኮ በጣም ቆሽሿል፤ ለምን አታፀዱትም?" ከማለቴ ያለ ምንም ዓይነት ደረሰኝ ገንዘብ የሚሰበስቡት እኚህ ሴትዮ የምንተዋወቅና የግል ቂም ያለን ሁሉ እስኪመስል ድረስ ጮሁብኝ። "ኑ ላሳይዎት" አልኳቸው። "በቃ ውጣ፤ እንደውም ያንተን ገንዘብ አልቀበልም" (አልተቀበሉኝም) አሉኝ። ወዲያው ምንም ሳይቆዩ ሱስ እያገላበጠ ልባቸው እስኪጠፋ የተጫወተባቸው የሚመስሉ ሁለት ጎረምሶች መጡና እንድወጣ ሊያስገድዱኝ ሞከሩ።

ከእነሱ ጋር ምንም ሃሳብ ሳልለዋወጥ ገንዘብ ተቀባይዋን ሴትዮ "እሺ ይህንን መናኸሪያ የሚያስተዳድረው ሰው ቢሮው የቱ ጋ ነው?" ስላቸው "ፓርላማ ነው፤ ሂድ ፓርላማ ጠይቅ" አሉኝ (ምናለ "የአዲስ አበባ ከተማ ፅዳት ኤጀንሲ ሂድ" እንኳን ቢሉኝ፤ ወይም ወደ ከተማው ጤና ቢሮ)። ይሄ ሁሉ ሲሆን ከአንድ ተጠቃሚ ሰው በስተቀር ከጎኔ የቆመ ሰው አልነበረም። ይህ ሰው "ከዚህ ሁሉ ጭቅጭቅ እኮ እናፀዳዋለን ብትሉ ጥሩ ነበር። ማፅዳቱ አይሻልም?" በማለት ነበር ሃሳቤን የተጋራው።

ባጭሩ ገንዘብ መሰብሰቡ ብቻውን ምንም እንደማይፈይድ፤ መፀዳጃ ቤቱ በዚህ ከቀጠለ ከነጭራሹም ሊዘጋ እንደሚችልና የራሳቸውን ገቢ እንደሚያሳጣ፤ ለራሳቸውም ቢሆን የሚበጀው ከሽረሪት ድር ጀምሮ ያለውን ጉድ ማስወገድ መሆኑን ተናግሬ ወደ እምሄድበት ሄድኩኝ።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ዘመናዊ የመፀዳጃ ቤቶችን (ከመለስተኛ ካፌዎች ጋር) በተለያዩ ቦታዎች በማስቀመጥ ከዚህ በፊት የሠራው ሥራ የሚያስመሰግነው ነው። በእነዚህ መፀዳጃ ቤቶች ገንዘብ የማስከፈሉ ተግባር ያለ ሲሆን ለየት የሚያደርጋቸውና ተቃውሞ የማያስነሳባቸው ገንዘብ ተቀባዮቹ መፀዳጃ ቤቶቹን በሚገባ ማፅዳታቸው ነው። በተለይም ተግባሩ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የዘላቂ ልማት ስድስተኛው ግብ፣ ‹‹የውኃና የንፅህና አጠባበቅ አቅርቦትንና ዘላቂነትን ማረጋገጥ ለሁሉም›› ዓላማን ከመያዙ፤ እንዲሁም፣ ቀጣዩ ግብ፣ ‹‹በየቦታው መፀዳዳትን ማቆምና የንፅህና አጠባበቅ ተደራሽነትን ማረጋገጥ›› ማለቱ ሲታወስ ከላይ የተደረጉትን በአድናቆት ማንሳት ተገቢ ይሆናል። እዚህ ላይ አሁን በልማት ምክንያት እየፈረሱ ያሉትን በፍጥነት የመተካቱ ነገርም ሊታሰብበት የሚገባ መሠረታዊ ጉዳይ ነው።

# ስፖርት





## ሠራተኛው የበጋ ወራት ውድድር በጠንካራ ፉክክር ቀጥሏል

ቦጋለ አበበ

በኢትዮጵያ ሠራተኛ ማህበራት ኮንፌዴሬሽን አዘጋጅነት በየዓመቱ የሚካሄደው የሠራተኞች የበጋ ወራት የስፖርት ውድድር ዘንድሮ ከጥር 19/2016 ጀምሮ በኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ በተደረገ የመክፈቻ ሥነሥርዓት መጀመሩ ይታወቃል፡፡ በጠንካራ ፉክክርም ቀጥሏል።

በአስር የስፖርት አይነቶች ከሰላሳ በላይ የሠራተኛ ስፖርት ማህበራትን እያፎካከረ የሚገኘው ይህ ውድድር ለስድስት ወራት ያህል የሚቆይ ሲሆን፤ ባለፉት ሳምንታት ጠንካራ ፉክክሮች ሲደረጉበት ቆይተል፡፡

ዘወትር በእረፍት ቀናት ቅዳሜና እሁድ በተለያዩ የስፖርት አይነቶች በበርካታ የማዘውተሪያ ስፍራዎች የሚካሄደው የሠራተኞች የበጋ ወራት ውድድር ባለፈው ሳምንት መርሀ ግብሩ ጠንካራ ፉክክር እያስተናገደ መቀጠሉን የኢሰማኮ የስፖርት ክፍል ኃላፊ አቶ ዮሴፍ ካሳ ተናግረዋል፡፡



በሠራተኛው ስፖርት ጠንካራ ፉክክር ከሚታይባቸው ውድድሮች አንዱ ቮሊቦል ነው፣

በሠራተኛው ስፖርት አጓጊ ፉክክር ከሚደረግባቸው ስፖርቶች አንዱ የሆነው በወንዶች እግር ኳስ ባለፈው ሳምንት ስድስት ጨዋታዎች ተካሂደዋል፡፡ አዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ የኢትዮጵያ አየር መንገድን ሰፊ በሆነ የ7ለ1 ውጤት የረታበት ጨዋታ አንዱ ሲሆን፤ መከላከያ ኮንስትራክሽን ሙገር ሲሚንቶን 5ለ1 ያሸነፈበት ጨዋታም በርካታ ግቦች የተመዘገቡበት የሳምንቱ መርሀ ግብር ነበር፡፡ በተመሳሳይ የኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ከ ሞዔንኮ ኩባንያ ያደረጉት ጨዋታ ጠንካራ ፉክክር በማስተናገድ ሰባት ግቦች ከመረብ ያረፉበት ሲሆን፤ባህር ትራንስፖርት 4ለ3 በሆነ ውጤት ማሸነፍ ችላል፡፡ ኢትዮጵያ ግብርና ሥራዎች ከ ኢስት አፍሪካ ቦትሊንግ ያደረጉት ጨዋታም ተመጣጣኝ ፉክክር የታየበትና 2ለ2 በአቻ ውጤት የተጠናቀቀ ነው፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ አውቶቡስ ደግሞ ኢትዮ ቴሌኮምን 4ለ1 ማሸነፍ ችሏል፡፡

በሠራተኛው ውድድር እንደ እግር ኳሱ ሁሉ ጥሩ ፉክክርና ጨዋታ የሚታይበት የቮሊቦል ውድድርም በሳምንቱ መርሀ ግብር በወንዶች ሁለት ጨዋታ አስተናግዷል፡፡ በዚህም አዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ሙገር ሲሚንቶን 3ለ0 ሲያሸንፍ፤ አዲስ አበባ ከተማ አውቶቡስ የኢትዮጵያ ግብርና ሥራዎችን 3ለ1 መርታት ችሏል፡፡ በሳምንቱ በቤት ውስጥ ውድድሮች ከተከናወኑ ፉክክሮች አንዱ በሆነው የጠረጴዛ ቴኒስ ውድድር በወንዶች ሦስት ጨዋታዎች ተካሂደዋል፡፡ ብራና ማተሚያ አዲስ አበባ አውቶቡስን 3ለ0 በሆነ የፎርፌ ውጤት አሸናፊ የሆነበትን ነጥብ ሲያገኝ፤ ኢትዮ ኤሌክትሪክ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክን 3ለ0 አሸንፏል፡፡ ተመጣጣኝ ፉክክር የታየበት የኢትዮጵያ ግብርና ሥራዎችና የሞዔንኮ ጨዋታ በግብርና ሥራዎች 3ለ2 አሸናፊነት ተጠናቋል፡፡ በተመሳሳይ ስፖርት በሴቶች መካከል በተካሄደው ብቸኛ ጨዋታም ኢስት አፍሪካ ቦትሊንግ ኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎችን 3ለ2 ያሸነፈበት ውጤት ተመዝግቧል፡፡

በሴቶች የዳርት ውድድር ኢትዮ ቴሌኮም ኢትዮጵያ ልማት ባንክን 2ለ0፣ ጂኦ ሴንቴቲክ ኢንዱስትሪያል አዲስ አበባ አውቶቡስን 2ለ1 ሲያሸንፉ በወንዶች ተመሳሳይ ውድድር አዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ብሔራዊ አልኮልና አረቄ ፋብሪካን በተመሳሳይ 2ለ1 ማሸነፍ ችሏል፡፡

በአዝናኝ ፉክክርና ትዕይንቶች የሚደምቀው የሠራተኛ የበጋ ወራት ውድድር ነገና ከነገ በስቲያ በሚከናወኑ የተለያዩ ውድድሮች የሚቀጥል ሲሆን፣ በሴቶች ቮሊቦል ኢትዮ ቴሌኮም ከመከላከያ ኮንስትራክሽን ነገ በዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት የሚያደርጉት ጨዋታ ይጠበቃል፡፡ በተመሳሳይ ቦታ ኢትዮ ቴሌኮም በወንዶች ቮሊቦል ቃሊቲ ብረታብረትን ሲገጥም፤ ኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ስራዎች ከፋፋ ምግብ ጋር ይጫወታል፡፡

ነገ ሜክሲኮ በሚገኘው የሙብራት ኃይል ክበብ የሚካሄዱ አራት የጠረጴዛ ቴኒስ ውድድሮችም ተጠባቂ ናቸው፡፡ በሴቶች አዲስ አበባ አውቶቡስ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሲገናኙ፣ በወንዶች ሞኤንኮ ከብሔራዊ አልኮልና አረቄ ፋብሪካ፣ ኢትዮጵያ ግብርና ሥራዎች ከፋፋ ምግብ፣ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከአዲስ አበባ አውቶቡስ ጨዋታቸውን ያደርጋሉ፡፡ ነገ በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት በሚካሄደው የከረንቦላ ውድድርም ሁለት ጨዋታዎች ይደረጋሉ፡፡

በሠራተኛው ዘንድ በጉጉት የሚጠበቀው የእግር ኳስ ውድድር ከነገ በስቲያ ሲደረግ በአንደኛ ዲቪዚዮን ሦስት ጨዋታዎች ተጠባቂ ናቸው፡፡ ኢትዮ ቴሌኮም ከዮሐንስ ቢፍ፣ አዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሚያደርጉት ጨዋታ ከጠዋቱ 3፡00 ጀምሮ በኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ ይካሄዳል፡፡ በተመሳሳይ ዲቪዚዮን አዲስ አበባ ከተማ አውቶቡስን ከኢትዮጵያ ክፍያ መንገዶች የሚያገናኘው አንድ ጨዋታ ደግሞ በጎፋ ካፕ ይከናወናል፡፡ በተመሳሳይ ሜዳ በሁለተኛ ዲቪዚዮን አዋሽ ወይን ፋብሪካ ከፍል ውሃ አገልግሎት የሚያደርጉት ጨዋታም ይጠበቃል፡፡


## የግልፅ ጨረታ ማስታወቂያ
## ቁጥር 002/2016

በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት የአስኮ አዲስ ሰፈር የመጀ/ና መካከለኛ ደ/ት/ቤት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን እቃዎች በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት፣ማስጠገን እና ማሰራት ይፈልጋል፡፡

ሎት-1 አላቂ የቢሮ እቃዎች እና አላቂ የትምህርት ዕቃዎች
ሎት-2 የጽዳት ዕቃዎች
ሎት-3 የደንብ ልብስ
ሎት-4 ቋሚ መገልገያ እቃዎች እና መሣሪያዎች
ሎት-5 አላቂ የህክምና እቃዎች
ሎት-6 አላቂ እቃዎች
ሎት-7 የተለያዩ ስራዎች

ከላይ በተዘረዘሩት ሎቶች መሰረት፡-

1. በዘርፉ ህጋዊ የታደሰ ንግድ ፍቃድ ያላቸው እና የዘመኑን ግብር የከፈሉ መሆናቸውን ማረጋገጫ ማቅረብ የሚችሉ
2 የአቅራቢዎች የምዝገባ የምስክር ወረቀት እና የቫት ተመዝጋቢ የሆነ
3. ተጫራቾች ዝርዝር የጨረታውን ሰነድ ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ዘወትር በሥራ ሰዓት ከ2፡30-11፡30 ሠዓት ድረስ የጨረታ ሰነዱን የማይመለስ 100.00 ብር ብቻ /አንድ መቶ ብር / በመክፈል ከግዥአስተዳደር ቢሮ ቁጥር R-30 መውሰድ ይችላሉ፡፡
4. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ለእያንዳንዱ ሎት በሰንጠረዡ ሥር በተቀመጠው ዝርዝር በባንክ የተረጋገጠ ሲፒኦ (CPO) በማሰራት ማስያዝ ይጠበቅባቸዋል፣ ተጫራቾች ማስረጃቸውንና የእቃዎቹን (የስራዎቹን) ዋጋ ኦርጅናል እና ኮፒ (ቅጂ) ብሎ በመለየት ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 10 የስራ ቀናት ውስጥ ለዚህ ተብሎ በተዘጋጀ ሳጥን ውስጥ ማስገባት አለባቸው፡፡

| ሎት | የእቃው/የሥራው /ዓይነት | የጨረታ ማስከበሪያ የብር መጠን |
|---|---|---|
| 1 | አላቂ የቢሮ እቃዎች እና አላቂ የትምህርት ዕቃዎች | 1,000.00 |
| 2 | የጽዳት ዕቃዎች | 1,000.00 |
| 3 | ቋሚ መገልገያ እቃዎች እና መሣሪያዎች | 1,000.00 |
| 4 | የደንብ ልብስ | 1,000.00 |
| 5 | ለአላቂ የህክምና እቃዎች | 1,000.00 |
| 6 | ለአላቂ እቃዎች | 1,000.00 |
| 7 | የተለያዩ ስራዎች | 2,900.00 |

5. ማንኛውም ተጫራች በጨረታ ከቀረበው አጭር መግለጫ /specification/ ውጪ በመሰረዝ ወይም በማሻሻል ማቅረብ እና በሌላ ዋጋ ላይ ተንተርሶ መጫረት አይፈቀድም እንዲሁም ሙሉ የጨረታ ሰነድ ተመላሽ ይደረጋል፡፡
6. ከጥቃቅን እና አነስተኛ ተደራጅተው በጨረታው መሳተፍ የሚፈልጉ ተጫራቾች በትምህርት ቤቱ ሥም የተፃፈ ደብዳቤ እና የጨረታውን ቁጥር ጠቅሰው በመጻፍ መሳተፍ ይችላሉ፡፡
7. ተጫራቾች ጨረታውን ካሸነፉ የውል ማስከበሪያ (CPO) 10% ያስይዛሉ፡፡
8. የጨረታው ሳጥን በ10ኛው ቀን 11፡00 ሠዓት ታሽጎ በ11ኛው ቀን በ4፡30 ሠዓት በት/ቤቱ መሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ ይከፈታል፤ ነገርግን የሚከፈትበት ቀን ካላንደር የሚዘጋው ቅዳሜ እና እሁድ ወይም ሀገር አቀፍ ክብረ በዓል ከሆነ በሚቀጥለው ቀን ይከፈታል፡፡
9. ተጫራቾች በሚወዳደሩበት ሎቶች ላይ ናሙናዎችን ጨረታው ከመከፈቱ በፊት ማቅረብ አለባቸው፡፡
10. የጨረታ አሸናፊ ድርጅት ያሸነፈውን ዕቃ በራሱ የትራንስፖርት ወጪ መ/ቤቱ ድረስ የማቅረብና የማስረከብ ግዴታ አለበት፡፡
11. ት/ቤቱ ለጨረታ ከቀረበው ዕቃ እስከ 20% የመቀነስም ሆነ የመጨመር መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
12. ት/ቤቱ የተሻለ ዘዴ ካገኘ ጨረታውን በሙሉ ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
13. ሎት 7ን በተመለከተ ተጫራቾች ዋጋ የሚያቀርቡት ለስራዎቹ የሚያገለግሉ እቃዎችን እና አጠቃላይ የጉልበት ዋጋን ጨምሮ ነው እንዲሁም ዋጋ ከመሙላታቸው በፊት ስራዎቹን በአካል በመቅረብ መመልከት ግዴታ ሆኖ ማየታቸውን የሚያረጋግጥ ፊርማ ማኖር ይኖርባቸዋል።

አድራሻ፡-አስኮ አዲስ ሰፈር የመ/ደ/ት/ቤት አስኮ ሊዝ መንደር ቆዳ ሜዳ አጠገብ ይገኛል (የቀድሞ ረታ ት/ቤት)፡፡
ለተጨማሪ መረጃ ስ/ቁጥር 011-2-73-14-41 ወይም 011-2-73-08-02 ወይም 011-73-19-38

**በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት የአስኮ አዲስ ሰፈር የመጀ/ደረጃና መካከለኛ ደ/ት/ቤት**



## የጨረታ ማስታወቂያ

የደራርቱ ቱሉ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በ2016ዓ.ም አገልግሎት ላይ የሚውሉ የተለያዩ እቃዎች ማለትም ፡-

- የደንብ ልብሶች
- አላቂ የቢሮ ዕቃዎች
- አላቂ የትምህርት ዕቃዎች
- አላቂ የፅዳት ዕቃዎች
- ልዩ ልዩ መሣሪያዎች
- ቋሚ እቃዎችን

በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል በዚህ መሰረት ተጫራቾች፡-

1. በመንግስት ዕቃ አቅራቢነት ተመዝግበው የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ እና ቫት ተመዝጋቢ ለመሆናቸው ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ፡፡
2. ተጫራቾች በዘርፉ ወይም በመስኩ የታደሰ ንግድ ፍቃድ ያላቸው መሆን አለባቸው፡፡
3.የዘመኑን ግብር የከፈሉና ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ፡፡
4.ተጫራቾች ተጨማሪ እሴትታክስ ተመዝጋቢ ለመሆናቸው ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ፡፡
5.ተጫራቾች ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10 ተከታታይ የስራ ቀናት ዘወትር በስራ ሰዓት በትምህርት ቤቱ ፋይናንስ ቢሮ ቁጥር10 ብር 200.00 /ሁለት መቶ ብር/ በመክፈል የጨረታውን ሰነድ መግዛት ይችላሉ፡፡
6.ተጫራቾች የሚጫረቱበትን ዋጋ በገዙት ሰነድ ላይ ባለው የዋጋ ማቅረቢያ ቦታ በግልጽ በመሙላት በመጨረሻ ቦታ ላይ ስም ፡ ፊርማና ህጋዊ ማህተም በማኖር በታሸገ ኢንቨሎፕ ዋናውን እና ፎቶ ኮፒውን በማሸግ ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10 ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ ዘወትር በስራ ሰዓት ከ2፡00-11፡00 ዋጋቸውን በመሙላት በተጠቀሰው የስራ ሰዓት የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይችላሉ፡፡
7.ለጨረታ ማስከበሪያ የሚሆን የሚወዳደሩበትን ዋጋ በሲ.ፒ.ኦ ብር 2% (ሁለት ፐርሰንት) ማስያዝ ይኖርባቸዋል፡፡
8. ተጫራቾች ናሙና ለሚያስፈልጋቸው እቃዎች ጨረታው ሊዘጋ አንድ ቀን እስኪቀረው ድረስ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
9. ጨረታውን አሸናፊ ሆነው ከተገኙ በኋላ 10% ባሸነፉበት ዕቃ መጠን መሰረት የውል ማስከበሪያ ማስያዝ ይኖርቦታል፡፡
10. ጨረታውን ለማዛባት የሚሞክር ከጨረታው ውጪእንደሚሆንና የጨረታውን ማስከበርያ CPO እንደሚወረስባቸው ማወቅ አለባቸው፡፡
11. ጨረታው የሚከፈተው ተጫራቾች እና ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ጨረታው በተዘጋ በቀጣዩ የስራ ቀን ከቀኑ በ5፡00 ሰዓት በትምህርት ቤቱ ግዢ ንብረት አስተዳደር ጠቅላላ አገልግሎት ኬዝ ቲም ቢሮ ቁጥር 10 ይከፈታል፡፡
12. መስሪያ ቤቱ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
13, ለበለጠ መረጃ በስልክ ቁጥር፡-0114343278/ 0114715349

አድራሻ፡- በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ ስምንትከቃሊቲ ቶታል ዝቅ ብሎ ከአሮጌው አስፓልት 200 ሜትር ገባ ብሎ

**የደራርቱ ቱሉ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት**